# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 335 ነሐሴ 5 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

# ሕወሓት ትምህርት ቤቶችን ያወደመው ሌላውን በማደንቆር ለብቻው ለመግዛት ካለው ምኞት እንደሆነ ተገለጸ

## - ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉ 15 ሺህ መጽሐፍት ለአብርሆት ተበርክቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት ትምህርት ቤቶችን ያወደመው ሌላውን በማደንቆር ለብቻቸው ለመግዛት ካለው ፍላጎት እንደሆነ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ ገለጹ። በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ያሉ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ አባላት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያገለግሉ የሚችሉ 15ሺህ መጻሕፍትን ለአብርሆት ቤተመጽሐፍት አስረክበዋል።

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ ከአራት ሺህ 800 በላይ ትምህርት ቤቶች በሽብር ቡድኑ ጉዳት እንደደረሰባቸው በመጥቀስ፤ ቡድኑ ይህንን ያደረገው ለብቻቸው መግዛት የሚችሉት ሌላውን በማደንቆር ብቻ እንደሆነ ስለሚያስቡ ነው ብለዋል።

ሚኒስትሩ እንደገለጹት፤ ሕወሓት በጦርነቱ ወደ አንድ ሺህ 300 ትምህርት ቤቶችን ሙሉ ለሙሉ አውድሟል። ሦስት ሺህ በሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ደግሞ

ሕወሓት ትምህርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ከፋይል

# 177 ሺህ የሚጠጉ መዝገቦች እልባት ማግኘታቸውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2014 በጀት ዓመት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች 176 ሺህ 797 መዝገቦች እልባት ማግኘታቸውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስታወቀ።

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መዓዛ አሸናፊ ትናንት ባለፈው በጀት ዓመት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በተከናወኑ አበይት ተግባራትና በተገኙ ውጤቶች ላይ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ የዳኝነት ነጻነት፣ የአገልግሎት ቅልጥፍና፣ ጥራት ያለው የዳኝነት አገልግሎት እና የዳኝነት ተጠያቂነት በበጀት ዓመቱ በትኩረት ከተሰራባቸው ጉዳዮች መካከል ናቸው።

በዚህም በበጀት አመቱ 176 ሺህ 797 መዝገቦች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እልባት ማግኘታቸውን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቷ፤ ይህ አፈጻጸም ከ2013 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸርም በ5 ሺህ 521 መዛግብት አብላጫ አለው ብለዋል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ2014 ዓ.ም የዳኝነት ነፃነት እንዲከበር ውጤታማ የሪፎርም ሥራዎችን እንደሠራ ፕሬዚዳንቷ

177 ሺህ የሚጠጉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# «የሕዝባቸውን የልብ ትርታ የሚረዱ ሰዎች ቀርበው ኮሚሽኑን መርዳት ይኖርባቸዋል»

- ኡስታዝ ጀማል በሽር

ማሕበራዊ ሚዲያ አንቂና የአባይ መብቶች የኢትዮጵያ ተሟጋች

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝባቸውን የልብ ትርታ የሚያውቁ የሃይማኖት እና ሲቪክ ማኅበራት ወካዮች ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑን ቀርበው መርዳትና መደገፍ እንደሚኖርባቸው ኡስታዝ ጀማል በሽር ገለጹ።

የማህበራዊ ሚዲያ አንቂና የአባይ መብቶች

«የሕዝባቸውን የልብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## ስምክክሩ ሀገራዊ እሴቶችን እንደመሳሪያ መጠቀም እንደሚገባ ተገለፀ

ገጽ 4

ዜና

# አካዳሚው ብቁ አመራሮችን ለማፍራት በትኩረት እየሠራ መሆኑን ገለጸ

## - በመጪው ዓመት ማስተማር እንደሚጀምርም አስታውቋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የተሰጠውን ተልዕኮ እውን ለማድረግ ተቋምን፣ ከተማንና አገርን ሊለውጡ የሚችሉ ብቁ አመራሮችንና ባለሙያዎችን ለማፍራት በትኩረት እየሠራ መሆኑን ገለጸ። በ2015 የትምህርት ዘመን ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅት እያደረገ መሆኑንም አስታውቋል።

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ደሳለኝ ጴጥሮስ በከተማ አመራርና አስተዳደር ትምህርት ካሪኩለም ላይ ግብዓት ለመሰብሰብ በተዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ አዳሚው ተቋምን፣ ከተማንና አገርን ሊለውጡ የሚችሉ ብቁ አመራሮችንና ባለሙያዎችን እንዲያፈራ የተሰጠውን ተልዕኮ እውን ለማድረግ በትኩረት እየሠራ ነው።

አዲስ አበባ የበርካታ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ተቋማት መቀመጫ ናት ያሉት ዶክተር ደሳለኝ፤ በመሆኑም ይህንን በሚመጥን መልኩ ከተማዋን ሊመራ የሚችል አመራር ምን አይነት ትምህርትና ስልጠና ያስፈልገዋል የሚለውን ለመመለስ እየሠራ ነው ብለዋል።

አዲስ አበባ ከተማ ላይ ያልተመጣጠነ እድገት ይስተዋላል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህን ችግር ለመቅረፍና ከተማዋን የሚመጥን ብቃት ያላቸው ብቁ አመራሮችና ባለሙያዎችን ለማፍራት ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ያካተተ የትምህርት ካሪኩለም መቀረጹንም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ከ900 በላይ ከተሞች ቢኖሩም ብዙዎቹ በፕላን የሚመሩ አለመሆናቸውን ጠቁመው፤ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመንና የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስ አመራሩ በክህሎት፣ በእውቀትና በስነምግባር የበለጸገ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ስድስተኛውን አገራዊ ምርጫ ተከትሎ አካዳሚው በአዲስ መልክ መቋቋሙን የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህም በትምህርት፣ በማህበረሰብ አገልግሎት፣ በስልጠናና በማማከር አመራሩና ባለሙያውን እንዲያበቃ ትልቅ ኃላፊነት ተጥሎበታል ሲሉም ተናግረዋል።



ዶክተር ደሳለኝ ጴጥሮስ



ዶክተር ለሚ ተስፋ

ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሦስት የትምህርት መስኮች የካሪኩለም ጥናት መከናወኑን ያስታወሱት ዶክተር ደሳለኝ፤ በቀጣይ ጥር ወር በከተማ አመራርና አስተዳደር ትምህርት መስክ በሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

አካዳሚው በ10 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ እየገነባ ያለው ዘመናዊ ማሰልጠኛ በቅርብ ጊዜ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመው፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ የአካዳሚውን አቅም በእጅጉ ከፍ ያደርገዋል ሲሉም ጠቁመዋል።

የአካዳሚው የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ለሚ ተስፋ በበኩላቸው፤ አካዳሚው የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን እንዲሰጥና የማማከር አገልግሎት እንዲያከናውን ኃላፊነት ተሰጥቶታል ብለዋል።

አካዳሚው ከተማዋ ላይ ትልቅ የአመራር ክፍተት መኖሩን ለይቷል ያሉት ዶክተር ለሚ፤ ይህን ክፍተት በአጭር ጊዜ ውስጥ በመሙላት የተስተካከለ እድገትና ለነዋሪዎቿ የምትመች ከተማ ለመፍጠር መሥራት ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።

አዲስ አበባ ትልቅ የዲፕሎማሲና ሰፋ ያለ የንግድ እንቅስቃሴ የሚስተዋልባት ከተማ ናት ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከተማዋን ይበልጥ እያሳደጉ ለመሄድ አመራሩ በእውቀት፣ በክህሎትና በሥነ-ምግባር መታነጽ አለበት። ለዚህም ከተማዋ በሁሉም መልኩ ለኑሮ የምትመረጥ ከተማ እንድትሆን አካዳሚው የበኩሉን ሚና ለመወጣት እየሠራ ነው ብለዋል።

# በክልሉ ከ200 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ኩባንያዎች በማዕድን ዘርፍ ተሰማርተዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- አማራ ክልል ከ200 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ኩባንያዎች በማዕድን ኢንቨስትመንት ዘርፍ የምርመራና ማምረት ስራ ፈቃድ ወስደው እየሰሩ መሆናቸውን የክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ አቶ ኃይሌ አበበ እንደገለጹት፤ በክልሉ ያለውን ዕምቅ የማዕድን ሀብት በአግባቡ አልምቶ ጥቅም ላይ ለማዋል ቢሮው በትኩረት እየሰራ ነው። ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ብቻ ከ200 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ 102 ኩባንያዎች በማዕድን ዘርፍ የምርመራና ማምረት ስራ ፈቃድ ወስደው እየሰሩ ይገኛሉ።

የተለያዩ ፋብሪካዎች ለወለል ንጣፍ፣ ለደረጃና ሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ግራናይት፣ ማርብልና ጂብሰም እያመረቱ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

ኩባንያዎቹ በዓመት እስከ 130 ሺህ ቶን ግራናይት ማርብልና ጅብሰም አምርተው ለሀገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ መጀመራቸውን አመልክተው፤ ከውጭ ይገቡ የነበሩ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች የመተካት ስራ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

የምርመራ ፈቃድ ከወሰዱ ሰባት የሲሚንቶና 30 የድንጋይ ከሰል ኩባንያዎች 3ቱ የምርመራ ስራቸውን ማጠናቀቃቸውን ገልጸው፤ የማምረት ፈቃድ ወስደው ወደ ሥራ መግባታቸውን አመልክተዋል።

በማዕድን ዘርፍ የምርመራና የማምረት ፈቃድ የወሰዱት ኩባንያዎች ከ23 ሺህ ለሚበልጡ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠራቸውንም አቶ ኃይሌ አስታውቀዋል።

“ሀገሪቱ በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ወደ ከፍታ ከምትወጣባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ ማዕድን ነው” ያሉት አቶ ኃይሌ፤ የክልሉ መንግስትም ለዘርፉ ዕድገት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

የቤአይካ ጄኔራል ቢዝነስ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ምስጋናው በበኩላቸው፤ ኩባንያቸው 10 ቢሊዮን ብር በሚጠጋ ካፒታል በንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ እርሻና ኮንስትራክሽን ዘርፎች ተሰማርቶ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለይ በማዕድን ዘርፍ ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚውሉ ግራናይት፣ ማርብል፣ ታይልስና ካልሽየም በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ መቶ በመቶ እያመረቱ መሆኑን አስረድተዋል።

አሁን ላይ ግራናይት 3 ሺህ 500 ካሬ፣ ማርብል 1 ሺህ ካሬ፣ ታየርስ 2 ሺህ 500 ካሬ፣ ቀለም 100 ሺህ ሊትር በቀን በማምረት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ምርቱን ተደራሽ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

በሀገር ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት ለማሟላት እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከመጪው ጥቅምት ወር ጀምሮ የግራናይት ምርትን በሶስት ዕጥፍ፣ የማርብል ምርትን ደግሞ በሁለት ዕጥፍ የሚያሳድጉ ተጨማሪ ፋብሪካዎችን ለመትከል የተገዙ ማሽነሪዎችን እያጓጓዙ መሆኑን ኢዜአ ዘግቧል።

ለኤክስፖርት ብቻ የሚሆን የግራናይት ምርት የሚያመርት ግዙፍ ፋብሪካ ጥሬ ዕቃው በሚገኝበት በምዕራብ ጎጃም ቡሬ አካባቢ ለመትከል ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

“መንግስትም 24 ሰዓት ፋብሪካዎቻችን ስራቸውን ሳያቋርጡ እንዲያከናውኑ በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ከማቅረብ ጀምሮ የተለያዩ ድጋፎች እያደረገልን ነው” ብለዋል።

ኩባንያው በተሰማራባቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለ7 ሺህ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠሩን ጠቅሰው፤ ከዚህ ውስጥ 40 በመቶው በማዕድን ዘርፍ የተፈጠረ ነው ብለዋል።

በአማራ ክልል ለኢንዱስትሪ፣ ለኮንስትራክሽን፣ ለብረት፣ ለኃይል አቅርቦትና ለጌጣጌጥ የሚውሉ 35 አይነት ማዕድናት እንደሚገኙ በጥናት መረጋገጡን ከቢሮው የተገኘ መረጃ ያመላክታል።

# ክልሉን ከዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማስተዋወቅ እንደሚገባ ተገለጸ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ኦሮሚያ ክልል የበርካታ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ሀብት ባለቤት ቢሆንም በቱሪዝም ሀብት ተጠቃሚ ለማድረግ ዘርፉን የማልማትና ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራ ይበልጥ ሊሰራ እንደሚገባ ተገለጸ።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የቱሪዝምና ቴክኖሎጂ ሳምንት ትናንት የክልሉና የፌዴራል ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት በይፋ ተከፍቷል።

በመክፈቻ መርሃግብሩ ላይ የተገኙት የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ፤በክልሉ ያለውን የቱሪዝም ሀብት እድል በመጠቀም የዘርፉን ክፍለ ኢኮኖሚ በዘመነ መልኩ ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

የክልሉ ቱሪዝም ኮሚሽን ባለፉት ሁለት ዓመታት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በሰራው ስራ የክልሉ የቱሪዝም ሀብት በከፍተኛ ሁኔታ መነቃቃቱን አውስተው፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለቱሪዝም ዘርፉ በተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት በክልሉ ያሉ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማት እንዲሁም በማስተዋወቅ ረገድ የተሰሩ ስራዎች አበረታች ቢሆኑም ዘርፉን ለማሳደግ የበለጠ መሥራት እንደሚገባውና የግሉ ዘርፍ ሚናም ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል።

በአለም አቀፍ ደረጃ የቱሪዝም ዘርፉ ኢኮኖሚውና በሰው ኃይል ተጠቃሚነት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመምጣቱ ሀገራችን ሀገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን በተገቢው መጠቀምና ማሳደግ እንዲሁም ማስተዋወቅ እንደሚገባ የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ሀብት




ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

ቢኖራትም ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን የቱሪዝም ዘርፉን በማልማት እንዲሁም ዘመኑ የሚፈልገውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ቱሪዝሙን በዲጂታል ቴክኖሎጂ በማሳለጥ የማስተዋወቅ ስራ ይበልጥ ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የክልሉ የማህበራዊ ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱልሀኪም ሙሉ የሀገርን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ለቱሪዝም ዘርፉ ሚና ወሳኝ በመሆኑ ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ በጥራት፣ በፍጥነትና በቀላሉ ማድረስ ዘመኑ የሚጠይቀው ስራ እንደሆነ ተናግረዋል።

በዚህም በክልሉ የሚገኙትን የቱሪዝም መዳረሻዎች በማልማትና በማስተዋወቅ ሰፋፊ ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን ተናግረው፤ ወጣቶች ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ በመሰማራት ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር ለሊሴ ዱጋ የክልሉን ቱሪዝም ለማሳደግና ለማስተዋወቅ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ገልፀው፣ ኮሚሽኑ በዚህ ረገድ አዲስ ምዕራፍ በመክፈት ክልሉ ያለውን የቱሪዝም እድል ለመጠቀም እየሰራ መሆኑን አመልክተዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ ኮሚሽኑ የክልሉን ቱሪዝም ዘርፍ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማስዋወቅ ከጎግል አርት ኤንድ ካልቸር ጋር በመሆን በሚሠራውና ይህን ለማሳለጥ የሚረዳ ‘የጎግል አርት ኤንድ ካልቸር’ መተግበርያ ይፋ ሆኗል።

በመርሀ ግብሩ ላይ የኦሮሚያ የቱሪዝም መዳረሻዎችን የሚገልጹ ፎቶግራፎች፣ የኦሮሞ ባህል ቁሳቁሶችና ሌሎች በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የሚሰሩ የአስጎብኚ ድርጅቶች የስራ ውጤቶች ለጎብኚዎች ይፋ ሲሆኑ፤ መርሃግብሩ ለተከታታይ አራት ቀናት የውይይትና ምክክር እንዲሁም የማስተዋወቅ ስራ በመስራት እንደሚቆይ ታውቋል።

# ፍትሐዊ ውሳኔዎች እና አገልግሎት ለመስጠት ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ትኩረት እንደሚገባ ተገለጸ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፦ ፍትሐዊ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ ስርዓት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተገለጸ። “ወሳኝ ኩነትን በወቅቱ በማስመዝገብ ሁሉም ሰው የሚታወቅባት ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ” በሚል መሪ ቃል 5ኛው የወሳኝ ኩነት ምዝገባና ስታቲስቲክስ ቀን በትናንትናው ዕለት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ተከብሯል።

በክብረ በዓሉ ላይ የተገኙት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ ባስተላለፉት መልዕክት አገራዊ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ስታቲስቲክስ አገልግሎት መረጃዎችን በአገር አቀፍ ደረጃ ተደራሽና ሁሉን አቀፍ በሆነ ሁኔታ በቀጣይነት ለመሰብሰብ፣ ለማስተዳደር፣ ለማደራጀትና ጥቅም ላይ ለመዋል የሚያስችል ነው። ይህም ሁሉንም የአገሪቱን የአስተዳደር እርከኖች አስተማማኝ በሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ለማቀድ እና ለማስተዳደር ይረዳል።

የምዝገባ ስርዓቱ አገራችን በአሁኑ ወቅት ሰላሙ



አቶ ተስፋዬ በልጅጌ

የተረጋገጠ፣ የዘመነ እና የበለጸገ ማህበረሰብ ለመመስረት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን ለመተግበር በምታደርገው ጥረት ዋነኛ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል ብለዋል።

በኢፌዴሪ ህገመንግስት እና በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች እና ስምምነቶች ላይ የተቀመጡ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሚመለከታቸው አካላት መከበር አለመከበራቸውን ለማረጋገጥ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የሚገኝ መረጃ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑንም ገልጸዋል።

በኢፌዴሪ ህገመንግሰት ከዜግነት ጋር ተያይዞ አንቀጽ ስድስት ንዑስ አንቀጽ አንድ እንዲሁም ከሰብዓዊ መብት ጋር ተያይዞ ከአንቀጽ 14 እስከ 18 የተቀመጡ የህግ ድንጋጌዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ መረጃ ላይ ተመስርተው ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው፤ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶች ላይ የሚገኙ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች መረጃ ያለ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የተሟላ መረጃ ተግባራዊ አይሆኑም ብለዋል።

ለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስኬታማነት በየደረጃው የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጥረት የሚያስፈልግ መሆኑንም አስገንዝበዋል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ብሩህተስፋ ሙሉጌታ በበኩላቸው፤ የፀጥታ ችግር በሌለባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች በሚገኙ 16 ሺህ የምዝገባ ጣቢያዎች የሞት፣ የልደት፣ የፍቺ፣ የጋብቻ፣ የጉዲፈቻ ሁነቶችን መመዝገብ መቻሉን ገልጸዋል።

በተባበሩት መንግስታት 2030 እና በአፍሪካ 2063 መሪ እቅድ መሳካት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የወሳኝ ኩነት መረጃ ያስፈልጋል ብለዋል።

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ መረጃዎች አገራዊ እቅዶችን ለማቀድና ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ የሚያስችሉ በመሆኑ የሚሊንየሙ መሪ የእድገት እቅዶች ውስጥ ከተቀመጡት ግቦች አብዛኛዎቹ በወሳኝ ኩነት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የሚከናወኑ በመሆኑ ለትክክለኛ መረጃ ምንጭነት አቅም የሚፈጥር ነው ብለዋል።

ህብረተሰቡ በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤውን በማሳደግ ልደት በ90 ቀን ውስጥ ጋብቻ ፍቺ እና ሞት በ30 ቀን እንዲያስመዘግቡም ጥሪ አቅርበዋል።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው፤ በወሳኝ ኩነት ምዝገባ የተገኙ መረጃዎች ለእቅድ ዝግጅት፣ ለፍትህዊ የሀብት አጠቃቀም በተለይም በዜጎች ፍትሀዊ የጤና አጠቃቀም የመጀመሪያ የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ ብለዋል።

የሀገራችን የወሳኝ ኩነት ምዝገባ በአፍሪካ አገራት ደረጃ በዝቅተኛ አፈጻጸም ላይ የሚገኝ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ ሆኖም ሰነዱ በአገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ እቅዶች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ የሚውል የመረጃ ምንጭ በመሆኑ ትኩረት እንደሚያስፈልገው ጠቁመዋል።

# ለከተማዋ የቱሪዝም ዕድገት ልዩ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች እንደሚገነቡ ተጠቆመ

**አምሳሉ ፈለቀ**

አዲስ አበባ፦ በ2015 በጀት ዓመት ለሐዋሳ ከተማ ዕድገትና ቱሪዝም ልዩ ፋይዳና ትርጉም ያላቸው ፕሮጀክቶችን ለመገንባት መታቀዱን የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ።

የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ረዳት ፕሮፌሰር ጸጋዬ ቱኬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ የከተማ አስተዳደሩ ትልቁ ራዕይ ከተማዋን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ማድረግ ነው። ከዚህ ቀደም ከነበሩት የቱሪዝም ሀብቶች በተጨማሪም ሌሎች ከተማዋን የበለጠ ሊያሳድጉና ሊያስተዋውቁ የሚችሉ መዳረሻዎች ያስፈልጋሉ። 2015ዓ.ም በጀት ዓመትም አስተዳድሩ ለከተማዋ ዕድገትና ለቱሪዝም መዳረሻነት ልዩ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶችን ለመገንባት ታቅዷል።

በአዲሱ በጀት ዓመት በከተማዋ ለመገንባት ከታቀዱት ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ የታቦር ተራራ የማልማት ፕሮጀክት መሆኑን ጠቁመው፤ የሲዳማን ሕዝብ የትግል ታሪክ የሚያሳዩ ወደ ተራራው የሚያወጡ 130 ደረጃዎችና የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ዘመናዊ መዝናኛዎችም እንደሚገነቡም ገልጸዋል።

የከተማውንና አካባቢውን ኢኮ-ቱሪዝም በሚገባ በሚያሳይ መልኩ የሚገነባው የልማት ፕሮጀክት ግንባታም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቆ ለጎብኚዎች ክፍት እንደሚደረግ ተናግረዋል።

ሌላው በአዲስ መልክ ሊገነባ የታቀደው በሻሸመኔ በኩል ወደ ሐዋሳ ከተማ መግቢያ ያለው በር መሆኑን ጠቅሰው፤ወደ ከተማዋ መግቢያ በሩ የከተማዋን ውበት፣ እንዲሁም የሲዳማን ባህል፣ ታሪክና እሴት በሚያሳይ መልኩ በአካባቢው ካለው የሚሊኒየም ፓርክ ጋር አብሮ እንዲለማ የሚደረግ መሆኑን አስታውቀዋል።የማልማት ስራውም ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ተገንብቶ እንደሚጠናቀቅ ነው የገለጹት።

የሐዋሳ ሐይቅን ዳርቻ ለማልማት በተያዘው ፕሮጀክትም በበጀት ዓመቱ 7 ነጥብ 5 ኪሎ ሜትር የሚረዝም የሐይቁ ዙሪያ ይለማል ያሉት ከንቲባው፤ የዲዛይንና የጨረታ ሥራው ተጠናቅቆ በዚህ ዓመት ወደ ግንባታ ይገባል ብለዋል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ጸጋዬ ቱኬ ገለጻ፤ የከተማዋን መሠረተ ልማቶች የመዘረጋት ሥራ በመሰራቱ ከተማዋ በሰላም፣በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝምና በተለያዩ የልማት ዘርፎች ተመራጭነቷ እየጨመረ መጥቷል። በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት የከተማዋን ዕድገት የሚመጥኑ ውጤታማ ተግባራት ተከናውነዋል።

በከተማዋ ከዚህ ቀደም በርካታ ፕሮጀክቶች ቢጀመሩም ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘታቸው ሲጓተቱ የነበረበት ሂደት መኖሩን አውስተው። ይህን ችግር በማስቀረት ባለፉት ሁለት ዓመታት ነባር ፕሮጀክቶችም ሆኑ አዳዲሶቹ ተጀምረው በተያዘላቸው ጊዜና ጥራት እንዲጠናቀቁ በማድረግ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን ገልጸዋል።

በአዲሱ የበጀት ዓመትም ለከተማዋ ዕድገትና ቱሪዝም ልዩ ትርጉምና ፋይዳ ያላቸው አዳዲስ ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ በልዩ ትኩረት እንሠራለን ብለዋል።

በተጨማሪም የሐዋሳ ከተማን ደረጃና ውበት የሚጨምሩ የውስጥ ለውስጥ ዘመናዊ የእግረኛና ተሽከርካሪ መንገዶችና ሕንጻዎች መገንባትና በሕገ-ወጥ መንገድ የተያዙና የከተማዋን ውበት የሚያደበዝዙ ቤቶች በዘመናዊ መልክ እንዲገነቡ የሚደረግ መሆኑን አመልክተዋል።

በመንገድ ዳር በህገ ወጥ መንገድ በግለሰቦች የተያዙ ቦታዎችን የማስለቀቅ ሥራ መጀመሩንና በፕላን ማስከበሩ ሂደት መንገድ ዳር ቦታ ይዘው ሲሠሩ የነበሩትን እንዲነሱ የተደረጉ ግለሰቦች በየክፍለ ከተማው ተደራጅተው የሚሠሩበት አግባብ እየተመቻቸ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።


ዘመናዊ ከተሞች በፕላን መመራት አለባቸው የሚሉት የከተማዋ አስተዳደር ከንቲባ ረዳት ፕሮፌሰር ጸጋዬ ቱኬ፤ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመትም ከዚህ ቀደም በሕገወጥ መንገድ ተይዘው የቆዩ ቦታዎችን በማስመለስና የከተማዋን ጸጥታና ሠላም የሚያረጋግጡ ተግባራትን በማከናወን የከተማዋ አስተዳደር በፕላን እንዲመራ ተደርጓል ሲሉም ነው የገለጹት።

የሐዋሳ ከተማ በሀገራችን ፈጣን ዕድገት እያመጡ ከሚገኙ ከተሞች አንዷ በመሆኗ ለቱሪዝም ተመራጭ ከተማ እንደሆነች ይታወቃል።

# የኢትዮጵያን ልማት ለማፋጠን የዲያስፖራውን አቅም አሟጦ መጠቀም ይገባል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፦ የአገርን ልማት ለማፋጠን የዲያስፖራውን የገንዘብ፣ የዕውቀትና የክህሎት አቅም አሟጦ መጠቀም እንደሚገባ በድር ኢትዮጵያ ገለፀ።



አቶ አሕመድ ወርቁ

የበድር ኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት አቶ አሕመድ ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ዲያስፖራው ማኅበረሰብ የገንዘብ፣ የዕውቀትና የክህሎት እምቅ አቅም አለው። እንደሚኖርበት ሀገር የሚወሰን የችግር አፈታት ልምድን ያካበተ ነው። መንግሥት እነዚህን አቅሞች ለሀገር ልማት በሚያመጡበት መንገድ አሟጦ መጠቀም ይኖርበታል።

ዲያስፖራው ማኅበረሰብ በሀገሩ ጉዳይ ላይ የሚጨነቅ የማኅበረሰቡ አካል ነው ያሉት አቶ አህመድ፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያደርጋቸውን ተሳትፎዎች ይበልጥ አጠናክሮ እንዲቀጥል መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍና ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል።

ከዲያስፖራው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ከዳር ለማድረስ ገንዘብ በመደገፍ እና በዲፕሎማሲ ረገድ ጉልህ ሚና እየተወጣ መሆኑን አመልክተው፤ ከዚህ አንፃርም በድር ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሙስሊሞች ተቋም በህዳሴ ግድብ ዙሪያ ዕውነቱን ለዓለም ማህበረሰብ በማሳወቅ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ መስራቱንና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ረገድም በቁርጠኝነት ሲሠራ እንደቆየ ገልፀዋል።

በዋናነት በሀገራችን ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን የሰላምና የልማት ችግሮች እንዳሉ ይታወቃል። ዲያስፖራው ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ድጋፍ እና የዕውቀት ሽግግር በማድረግ የራሱን አስተዋፅዖ ያደርጋል ሲሉም ተናግረዋል። በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ተመሳይ ተሳትፎዎችን እንደሚያደርግ ይጠበቃል ሲሉም አብራርተዋል።

በአሁኑ ጊዜ ዲያስፖራው እንደ ሁለተኛ ዜጋ የመታየቱ ሁኔታ ተቀርፏል ያሉት አቶ አሕመድ፤ ዲያስፖራው ማኅበረሰብ በሚያገኘው አጋጣሚና ስራዬ ብሎ የሀገርን ገፅታ የሚገነቡ ተግባራት ላይ በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ዕድሉን እንዲጠቀም አደራ እላለሁ ብለዋል።

እንደ አቶ አህመድ ገለፃ፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የተወሰኑ የዴሞክራሲ ጭላንጭሎች በመታየታቸው ዲያስፖራው ማኅበረሰብ ይህን ዕድል ተጠቅሞ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ጀምሯል። በተለይ ደግሞ ሀገራዊ ምክክሩ ላይ ዲያስፖራውን ወደ ሀገር ውስጥ በመጋበዝ እንዲወያይ መደረጉ የሚያበረታታ ነው።

ሀገራዊ ምክክር ወሳኝ ነው የሚሉት አቶ አህመድ፤ አሁን የተጀመረው የሀገራዊ ምክክር ሂደት ተስፋ ሰጪ ነው ብለው እንደሚያምኑ ገልፀው፤የተለያዩ ሃሳቦችን ማንሸራሸር ከተቻለ እና ግለሰቦችም ይሁኑ ተቋሞች በጋራ ጉዳያቸው ላይ መወያየት ከቻሉ ሀገር ወደ ፊት መራመድ ትችላለች ሲሉ ተናግረዋል።

ይህን ማድረግ ካልተቻለ አሁን እየታዩ ያሉ ጥሩ ያልሆኑ ምልክቶች በሰውም በሀገርም ላይ ጥፋት እያጠፉ የሚቀጥሉ ስለሚሆን ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ነፃ ሆኖ እና ሁሉንም በሚያካትት መልኩ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ሥራዎችን ሊሠራ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ዲያስፖራው በሀገራዊ ምክክር ላይ ካለው ተሳትፎ በተጨማሪ በጦርነትና በተለያዩ ምክንያቶች የተጎዱና የተፈናቀሉ ዜጎችን ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው ለመመለስ ከመንግሥት ጎን በመሰለፍ እንዲሠራም መልዕክት አስተላልፈዋል።

መንግሥት ዲያስፖራው ላይ በሁሉም ዘርፍ በጣም ትልቅ አቅም እንዳለ ሊገነዘብ እንደሚገባ የገለፁት ፕሬዚዳንቱ፤ በሁሉም ዘርፍ ዲያስፖራው ተሳታፊ እንዲሆን ቢደረግ ብዙ ችግሮችን በቀላሉ መፍታት ይቻላል ሲሉ ገልጸዋል።

# ለምክክሩ ሀገራዊ እሴቶችን እንደመሳሪያ መጠቀም እንደሚገባ ተገለፀ

አስናቀ ፀጋዬ


አዲስ አበባ፡- ቀደም ሲል የነበሩ የመተሳሰብ፣ አብሮ የመኖር፣ የመተጋገዝ፣ የመተባበርና ሌሎች ሀገራዊ እሴቶችን ለሀገራዊ ምክክሩ እንደመሳሪያ መጠቀም እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ገለፀ።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በተለይም ለአዲስ ዘመን ሲገልፁ፤ ቀደም ሲል የነበሩና ሀገራዊ እሴቶችን ለሀገራዊ ምክክሩ በመሳሪነት መጠቀሙ ተገቢ መሆኑን አስምረዋል።

ሆኖም ግን እነዚህን እሴቶች ብቻ እያዜሙ ከመቀጠል የእሴቶቹ ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ፣ የት ጋ ጥፋት እንዳጋጠማቸውና የት ጋ ቀኝና ኋላ እንደዞሩ መመርመር እንደሚገባ ጠቁመዋል። ጥፋቱ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ግን ሁሉም ሰው ልብ ሊለው እንደሚገባም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያዊነት በሁሉም አካባቢ እኩል ይዘመራል ወይ? ምንድነው ችግር ያጋጠመው? ለምንድን ነው እንደዚህ አይነት አጀንዳዎች አንዳንድ ቦታ ላይ ጎልተው ሌሎቹ ጋር የሚኮስሱት? የዚህስ ምክንያት ምንድን ነው? ጥፋቱስ የት ጋ ነው? የሚሉትን ጉዳዮች ማጥናት ተገቢ መሆኑንም ዋና ኮሚሽነሩ ገልፀዋል።

የሩቆቹንና በቅርብ ጊዜያት ውስጥ የነበሩ መንግስታትን መራገም ብቻ ሳይሆን ዋናው ጉዳይ እነዚህ መልካም እሴቶች የታጠፉበትን ቦታ በትክክል ለይቶ ያሉትን እሴቶች ሁሉም ጋ ባለቤትነት እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚገባም ዋና ኮሚሽነሩ አመልክተዋል።


ፎቶ - ዳኜ አበራ

ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ

የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች በተለያዩ መድረኮች የሚናገሯቸውን ሀገራዊ እሴቶች ወጣቶችም የሚከተሏቸው ከሆነ ውጤታማ ናቸው ተብሎ መውሰድ እንደሚቻልና ይህ ውጤታማ ካልሆነ ግን ራሳቸውን መፈተሽ እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል። ለዚህም ደፋር ጥያቄና ደፋር መልስ እንደሚያስፈልግ ዋና ኮሚሽነሩ ገልፀዋል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የሚያደርገውም ከታች እስከላይ ድረስ ያሉ ኢትዮጵያውያን ስለኢትዮጵያዊነት ምን እንደሚሉ? አጀንዳዎቻቸው ምንድን ናቸው? ምን ማቅረብ ይፈልጋሉ? በምን አካባቢ መወያየት ይፈልጋሉ? የሚለውን በመረዳት እጅግ መሰረታዊ በሆኑ ችግሮች ዙሪያ በመወያየት መፍትሄ ማምጣት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የምክክር ኮሚሽኑ ዋነኛ ስራም ሀገራዊ እሴቶችን እንደመሳሪያ በመጠቀም ህዝቡ እንደተለመደው ከላይ ወደታች ብቻ ሳይሆን ከታች ወደላይ እንዲሰማና ሌሎች የጎንዮሽ ውይይቶችንም እንዲያደርግ ማስቻል መሆኑን አመልክተዋል።

ለዚህም በአንድ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብሎ የመነጋገርና የመደማመጥ ብሎም መግባባት ላይ መድረስ፤ መግባባት ላይ መድረስ ባይቻል እንኳን መግባባት ባልተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ በመግባባት ኢትዮጵያዊነትን ይዞ ለመቀጠል ኮሚሽኑ የተቋቋመ መሆኑንም ዋና ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል።

## ሕወሓት ትምህርት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መለስተኛ ጉዳት አድርሷል። በጠቅላላው ከአራት ሺህ 800 በላይ ትምህርት ቤቶች በሽብር ቡድኑ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

የተማረና ማሰላሰል ማሰብ የሚችል ምክንያታዊ የሆነ ማህበረሰብ ካለ ለአምባገነንነት አይመችም ያሉት ሚኒስትሩ፤ ቡድኑ ይህንን የፈጸመው ይሄን አገር ለብቻው መግዛት የሚችለው ሌላውን በማደንቆር ብቻ እንደሆነ ስለሚያስብ ነው ብለዋል። ሌላውን ያልተማረ አድርጎ ኢ ፍትሐዊ አገዛዝ ለማስፈን እንደሆነም ጠቅሰዋል።

ሚኒስትሩ፤ “ሕወሓት በጦርነቱ ካደረሰው ውድመት እጥፍ የሚሆነውን የፈጸመው የትምህርት ሥርዓቱ ላይ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ይህንንም ያደረገው የትምህርት ስርዓቱን ለመግደል ነው ብለዋል።

ለዚህ ጦርነት ወጣቱ ተነስቶ ጠብመንጃ ይዞ ወደ ጦር የሚሮጥበት አንዱ ምክንያት ከትምህርት ሥርዓቱ ማግኘት ያለበትን መሠረታዊ የሆነ ሞራል እንዳያገኝ ስላደረጉት ነው ብለዋል።

በአቡዳቢ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ቦርድ አባል ዶክተር አብዱልወሀብ አደም ፤ በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ያሉ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያገለግሉ የሚችሉና ጠቅላላ ዋጋቸው 1ነጥብ 5 ሚሊየን ዶላር የሆነ 15 ሺህ መጻሕፍትን አስረክበዋል። በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ያሉ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ የኢትዮጵያን ገጽታ ከማስተዋወቅ በተጨማሪ ዜጎችን መደገፍና መብታቸውን የማስከበር ሥራ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

ከዚህም ባሻገር የኢትዮጵያ መንግስት በሚያደርገው ጥሪ ድጋፎችን እያደረገ እንዳለና ኮሙኒቲው ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን 40 ሚሊየን ብር ድጋፍ ማድረጉን ጠቅሰዋል። ድጋፉ ወደ ፊት ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሐመድ እንድሪስ፤ አገልግሎቱ በ2014ዓ.ም 53 የዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ሥራዎችን ማከናወን እንደቻለ በመጥቀስ፤ በዚህም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራዎች ተሳትፎ እንደነበራቸው ገልጸዋል። በመካከለኛው ምሥራቅ ያለው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ጠንካራ ሥራ እየሰራ እንዳለ በመጠቆም፤ አሁን ላይ የተደረገው የመጽሐፍት ድጋፉ የዕውቀት፣ የክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን የሚያግዝ መሆኑን ገልጸዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታዋ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ በበኩላቸው፤ ዲያስፖራው አገር ጥሪ ባደረገች ጊዜ ፈርጀ ብዙ ድጋፍ በማድረግ ትልቅ ሥራ እያከናወነ መሆኑን ተናግረዋል። ከዲያስፖራው ማህበረሰብ የተበረከቱ መጻሕፍት ለተማሪዎችና ምሁራን አጋዥና ጠቀሜታውም ዘመን ተሻጋሪ በመሆኑ ምስጋና አቅርበዋል።

## 177 ሺህ የሚጠጉ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አመልክተው፤ የዳኝነት ገለልተኝነት እና ነጻነት የዳኞች የሥነ ምግባር ደንብ እና ሌሎች መመሪያዎች እንዲሻሻሉ ተደርገዋል ብለዋል። በተጨማሪም የዳኞች ያለመከሰስ መብት እንዲነሳ የሚያስችል ደንብ ፀድቆ ተግባራዊ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነት ሕዝብ ተኮር ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ የሥርዓተ ፆታና የሕፃናት መብትን የሚመለከቱ መመሪያዎችና ደንቦችን በማዘጋጀት ወደ ሥራም እንዲገቡ ተደርጓል ብለዋል።

በሱማሌና ሌሎች አካባቢዎች ተዘዋዋሪ ችሎቶች እንዲደራጁ እና እንደ ሀዋሳ ባሉ ከተሞች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲቋቋም ተደርጎ ዜጎች ባሉበት አገልግሎት እንዲያገኙ መደረጉንም ፕሬዚዳንቷ ጠቅሰዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፤ 2014 በጀት ዓመት ፍርድ ቤቶች በቴክኖሎጂ የመጠቀም፣ የማስተናገድና የማደራጀት ሥራ እንዲሰሩ የሚያስችሉ ተግባራት ተሠርተዋል። የፍርድ ቤት መሠረተ ልማት እና ሌሎች በርካታ ዝርዝር ሥራዎችም ተከናውነዋል።

የፍርድ ቤቶችንና ዳኞችን እንዲሁም የተገልጋዮችን እርካታና አገልግሎት አሰጣጥ የሚፈትኑ የሙስና፣ የነፃነትና የፍርድ ጥራት ጉዳዮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም ከ80 በመቶ በላይ መዝገቦች እልባት እንዲያገኙ መደረጉን ተናግረዋል።

ወይዘሮ መዓዛ በ2015 በጀት አመት ትኩረት የሚደረጉባቸው ጉዳዮችም የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎችን ማጠናቀቅ፤ የፍርድ ጥራትና የዳኝነት ነፃነት ሥራዎችን ማከናወን፤ የፍርድ ቤት መሠረተ ልማት ግንባታዎችን ማከናወን እንደሆኑም ተናግረዋል።



ኡስታዝ ጀማል በሽር

## «የሕዝባቸውን የልብ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የኢትዮጵያ ተሚጋች የሆኑት ኡስታዝ ጀማል በሽር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ እስካሁን እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በጣም የሚያስደስት ነው። የኮሚሽኑን ዓላማ ከግቡ ለማድረስና ውጤታማ ለማድረግ የሕዝባቸውን የልብ ትርታ የሚያውቁ የሃይማኖት እና ሲቪክ ማኅበራት ወካዮች ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑን በቅርበት መርዳትና መደገፍ አለባቸው።

አካታች በሆነ አገራዊ ምክክርና ውይይት የማይፈታ ችግር የለም ያሉት ኡስታዝ ጀማል፤ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ከስያሜ ጀምሮ መልካም የሆኑ የመነጋገር እና የመወያየት አንድምታ ያለው በመሆኑ ጥሩ ነገር የሚያመጣ መሆኑን ጠቁመዋል። ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ያመጣል ብሎ ሁሉም ተስፋ የጣለበት እንደሆነም ተናግረዋል።

ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በትክክል ሥራውን ሠርቶ በእርግጠኝነት አንድ ታላቅ ነገር ይፈጠራል ብዬ አስባለሁ ያሉት ኡስታዝ ጀማል፤ የሕዝባቸውን የልብ ትርታ የሚረዱና በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ዳያስፖራዎች ያዩትንና ያካበቱትን ልምድ ለኮሚሽኑ በማጋራት ለውጤታማነቱ አጋዥ አስተዋፅኦአቸውን ማበርከት እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

እንደ ኡስታዝ ጀማል ገለፃ፤ ዳያስፖራው ማኅበረሰብ አሁን የሚኖርባቸው የሰለጠኑና የለሙ ሀገራት ለዚህ የበቁት የተለያዩ ችግሮችን አልፈው ነው። በመሆኑም ዳያስፖራው የእነዚህን ሀገራት ተሞክሮ ለሀገሩ በማጋራት ሀገራዊ የምክክር ሥራውን ለሚመራው አካል ግብዓት መሆን መቻል ይኖርበታል። የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም ከመንግሥትና ከሌሎች አካላት ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ሕዝብ ላይ ከሠራ ወደፊት ጥሩ ነገር ይመጣል የሚል ተስፋ አለኝ።

ዳያስፖራው ማኅበረሰብ ኮሚሽኑን ቀድሞ ከመፈረጅ መቆጠብ አለበት ያሉት ኡስታዝ ጀማል፤ በሀገራዊ ምክክሩ ውስጥ እንደ አንድ አካል ራሱን ለመወከል መጣር እንደሚኖርበትም አብራርተዋል።

ኡስታዝ ጀማል ዳያስፖራው በኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ ብዙ ነገሮችን እያደረገ እና ሁሉም መስከ በአቅሙ ልክ እየተሳተፈ እንደሆነ ገልጸው፤ በተናጠል ከሚደረገው ተሳትፎ በተጨማሪ የሃይማኖት እና ሲቪክ ማህበራት አደረጃጀቶች ውስጥ በሀገራቸው ጉዳይ ላይ በጋራ በመሳተፍ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር የሚጥሩ አካላት ጎልተው መውጣት እንደሚኖርባቸው ገልፀዋል።

ቀደም ሲልም አሁን የኢትዮጵያን ሁኔታ አስመልክቶ ትክክለኛ መረጃዎችን በማሰራጨትና ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ የዳያስፖራው ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበር ኡስታዝ ጀማል ተናግረዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን ተንተርሰው በሀገሪቱ ያለውን ልማት ለማደናቀፍ የሚጥሩ ኃይሎችን አብሮ በመዋጋትና በሃሳብ በመሞገት ዳያስፖራው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉን ገልፀው፤ በሀገራዊ ምክክሩ ላይም ተመሳሳይ አቋም ወስዶ በንቃት መሳተፍ እንደሚጠበቅበት ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አሸባሪና ሕገ ወጥ ታጣቂዎችን ሥጋት ከማይሆኑበት ደረጃ ማድረስ የሁሉም ኃላፊነት ነው!

ኢትዮጵያ አሁናዊ የብልጽግና ጉዞዋ እንዲሁም በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ካላት ስትራቴጂካዊ ቁመና አኳያ በርካቶች በመልካምም፣ በክፉም ትኩረት ካደረጉባት ውለው አድረዋል። በዚህም መልካም አጋሮች ወዳጅነታቸውን ሲያጠናክሩ፤ ጠላቶች ደግሞ በውስጥም በውጭም የሽብር ኃይሎችን በማደራጀት ዕረፍት እንዳታገኝና እንዳትረጋጋ ቀን ከሌት እየሰሩ ይገኛል። በዚህም እንደ ሕወሓት፣ ሸኔ እና አልሸባብ አይነት የሽብር ቡድኖችን በአንድ ሰንሰለት በማስተሳሰር ኢትዮጵያን በውስጥም በውጭም እንዲወጉ ሆኗል። ይሁን እንጂ ለፍቅር እንጂ ለኃይል እጅ ሰጥታ የማታውቀው ኢትዮጵያ እነዚህን የሽብር ኃይሎች ልክ በማስገባት አደብ እያስያዘች ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ ቀጥላለች። የአሸባሪው ሕወሓት ተግባርና የደረሰበት ኪሳራ ለዚህ ዓብይ ማሳያ ነው።

ከሰሞኑም የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት በአሸባሪና የታጠቁ ቡድኖች ላይ እየተወሰደ ያለውን ርምጃ ገምግሞ ነበር። ከግምገማው በኋላ ባወጣው መግለጫ እንዳመለከተውም፤ ሽብር ቡድኖችን ከመደምሰስ አኳያ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛል። ለምሳሌ፣ በኦሮሚያ ክልል ሸኔን ለመደምሰስ የሚያስችሉ የሸዋ፣ የወለጋ፣ የጉጂ ኮማንድ ፖስቶች በማደራጀት መከላከያ፣ የክልሉ አመራርና የክልሉ የጸጥታ ኃይሎች በጋራ የተቀናጀ ሥምሪት ተካሂዶ 3 ሺህ 180 የሸኔ ታጣቂዎች በቁጥጥር ሥር ሲውሉ፤ እጅ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑት ተደምስሰዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአባ ቶርቤ፣ የአልሸባብና የጁንታው ሴሎችና ተባባሪዎችም በቁጥጥር ስር ውለዋል። በርካታ የነፍስ ወከፍና የቡድን መሣሪያዎች፣ ተተኳሾች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ገንዘብና ልዩ ልዩ ንብረቶች ተማርከዋል።

በአማራ ክልልም ሕግን ለማስከበር በተወሰደው የተቀናጀ የጸጥታ ኃይሎች፣ የአመራሩና የሕዝቡ ሥምሪት የጸጥታ ኃይሎችን በመከዳት ለሕገ ወጥ ታጣቂዎች ዐቅም ሲፈጥሩ የቆዩ እና በልዩ ልዩ ወንጀሎች ሲፈለጉ የከረሙ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተጠርጣሪዎች በሕግ ጥላ ሥር ውለዋል። በተመሳሳይ በክልሉ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ወግነው በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦችን እርስ በእርስ ለማጋጨት የሚሰሩ ታጣቂዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል። ሰፊ ሕዝባዊ ውይይቶች ተደርገውም በተገኘው ግብዓት መሰረት በ633 አመራሮችና ባለሙያዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል።

በአዲስ አበባ ከተማ የሕዝብን ጸጥታና ደኅንነት ከማረጋገጥ አንጻር ከ497 በላይ የሕወሓት፣ የሸኔ፣ የአልሸባብና ሌሎች አክራሪ ቡድኖች፤ እንዲሁም የጸጥታ ኃይሎች አልባሳት፣ ሐሰተኛ መታወቂያዎች፣ ማኅተሞች፣ ለሽብር ተግባር የተዘጋጁ ሰነዶች፣ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች፣ የጦር መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ለአሸባሪዎች ሊላኩ የነበሩ ተንቀሳቃሽ ስልኮች እና የባንክ ደብተሮች አብረው በቁጥጥር ሥር ውለዋል። በከተማዋ በተደረጉ የሕዝብ ውይይቶችም በሽብር እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ከዚህ በላይ ማጋለጥና መቆጣጠር እንደሚገባ ግንዛቤ ተይዟል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝም ሲንቀሳቀሱ የነበሩ 1ሺህ 826 ሕገ ወጥ ታጣቂዎችን በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሲሆን፤ 749 ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎች እና 5ሺህ 639 ተተኳሾች ከጠላት የተማረኩ ሲሆን፣ 9 ጀልባዎችና 65 የጠላት ካምፖችም ወድመዋል።

በተመሳሳይ በሶማሌ ክልል ከውጭና ከውስጥ የሚመነጩ የደኅንነት ሥጋቶችን ለመከላከል፣ ለመቋቋምና ለማስወገድ ወሳኝ ተግባራት ተከናውነዋል። በዚህም ሐምሌ 14 ቀን በአፍዴር ዞን በባሬና ጎት ጎት ወረዳዎች ሠርጎ ለመግባት የሞከረውን የአልሸባብ ኃይል ተከታትሎ ለመደምሰስ የክልሉ ልዩ ኃይል ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን፤ የክልሉ አመራር ሕዝቡን በማንቃት፣ በማሳተፍና በማደራጀት ጠላትን ለመደምሰስ ትምህርት ሰጪ እንቅስቃሴ አድርጓል። በሂደት የሀገር መከላከያ ሠራዊት የተሳተፈበት ኮማንድ ፖስት በማቋቋም በተካሄደ ኦፕሬሽን 813 አሸባሪዎች ተገድለው 79 ተማርከዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የጦር መሣሪያዎች፣ ተተኳሽ ጥይቶች፣ ፈንጂዎችና መገናኛ ሬዲዮኖች ተማርከዋል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በትግራይ ክልል ያለው ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ በድርድር እንዲፈታ መንግሥት አቅጣጫ መያዙና የጀመረው የተግባር እንቅስቃሴ ድርድሩ ውጤት እስኪያመጣ ድረስ ለመቀጠል መንግሥት ቁርጠኛ ነው። በዚያ አካባቢ ያለው የሥጋት ሁኔታም ከጸጥታ አካላት ዐቅም በታች መሆኑንና ክትትል እየተደረገበት ያለ ስለመሆኑ ነው የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት ያስታወቀው።

ምንም እንኳን እነዚህና መሰል የሽብር ቡድኖችን ውስጣዊና ውጫዊ ቅንጅት ፈጥረው ኢትዮጵያን ለማተራመስ እየተንቀሳቀሱ ያሉበትን ሂደት ከማክሸፍና ርምጃ ከመውሰድ አኳያ በፀጥታ ኃይሉ ጥምረት እና በሕዝቡ ተሳትፎ አመርቂ ውጤት እየተገኘበት ቢሆንም፤ ከሽብር ቡድኖች ባህሪ አንጻር የበለጠ ተቀናጅቶና ሕዝቡን አሳትፎ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ላፍታም ሊዘነጋ የሚገባው አይደለም። ምክንያቱም ህልውናውን በጦርነት ውስጥ የገነባው አሸባሪው ሕወሓት ከውስጥና ከውጭ ኃይሎች ጋር ተቀናጅቶ ሊያደርገው የሚፈልገውን ጥፋት የቀጠለ እንደመሆኑ፤ አሸባሪንና ሕገ ወጥ ታጣቂዎችን ሥጋት ከማይሆኑበት ደረጃ ማድረስ በአመራሩ፣ በጸጥታ አካላትና በሕዝቡ ቁርጠኝነትና መሥዋዕትነት ሊተገበር የሚገባው ጉዳይ ነው።

በተለይም ሴሉን በኢትዮጵያ ለመትከል እየተውተረተረ ያለው አልሸባብ ከውጭና ከውስጥ ኃይሎች ጋር ተቀናጅቶ የሥጋት መጠኑን ለመጨመር እንዳይችል፣ የተቀናጀ የጸጥታ ኃይሎችና የሕዝብ ሥምሪት ማካሄድና በቀጣናው ትርጉም ያለው ኃይል እንዳይሆን ማድረግ እጅጉን አስፈላጊ ነው። ይህ እንዲሆን ደግሞ በእያንዳንዱ አካባቢ የሚከናወነው ጸጥታንና ደኅንነትን የማረጋገጥ ተግባር የመላው ኢትዮጵያ ሰላም የሚያጸና መሆኑን ማመን ያስፈልጋል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የስንዴ ፖለቲካ - ‹‹አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን ያዥ››

**ታምራት ተስፋዬ**

በአለም አቀፍ ደረጃ ዳቦ ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ከሆኑ መሠረታዊ የምግብ ዓይነቶች አንዱ ነው። ጥንታዊና እጅግ ተወዳጅ ‹‹one of the world's oldest and most beloved foods›› ተብሎም በበርካቶች ዘንድ ይንቆለጳጰሳል። በነጋ በጠባ ከብዙ ቢሊየኖች ደጅና ጓዳ የሚዳረሰውና በገበያ ላይ ሲኖር የመኖር ሕልውናን የሚያረጋግጠው ዳቦ፣ሲታጣም ‹‹bread riots›› በመፍጠር ሥልጣንን እንደ ወተት የሚንጥ ፖለቲካ አዘል ተወዳጅ ምግብ ነው። በየትኛውም የዓለም ጥግ ተወዳጅ የሆነው ዳቦ ዋነኛ ግብአት ደግሞ ስንዴ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃም የተለያዩ አገራት ስንዴን ያመርታሉ። ከራሳቸው ተርፈው ለሌሎች ይተርፋሉ።

ዓለማችን በተለያዩ ወቅቶችና ክስተቶች የስንዴ ምርት ማግኘት አልሆን ብሏት ኅተራዋ ደርቆ ያውቃል። ይህን ተከትሎም የስንዴ ፖለቲካ ‹‹wheat politics››ን በተደጋጋሚ አስተናግዳለች። በአሁን ወቅትም በስንዴ ፖለቲካ እየታመሰች ትገኛለች። ምክንያቱ ደግሞ የዳቦ ቅርጫት የሚባሉትና ከዓለም የስንዴ ምርት የውጭ ንግድ ከ28 በመቶው በላይ ወይንም አንድ ሦስተኛ የሚሆነው ፍላጎት የሚያቀርቡት ዩክሬንና ሩስያ ከየካቲት አጋማሽ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ወደለየለት ጦርነት መግባታቸው ነው።

በሁለቱ አገራት ጦርነት ምክንያት የስንዴ ዋጋ በአስራ ሶስት ዓመታት ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ንሯል። ቀውሱም በበርካታ ሀገራት የምግብ እጥረትን በማስከተል ረሀብና ተቃውሞን ሊቀሰቅስ ይችላል የሚል ስጋት አሳድሯል። የቀውሱ ተጽእኖም በተለይም በሁለቱ አገራት ምርቶች ላይ ጥገኛ በሆኑት አገራት በርትቷል። ከሳውዲ አረቢያ እስከ ተርኪዬ፣ ከሱዳን እስከ ባንግላዴሽ፤ ከፓኪስታን እስከ እስራኤል፣ ከአዘርባጃን እስከ ቬትናም፣ ከኢንዶኔዥያንም እስከ ግብፅ እንዲሁም ሌሎች አገራት የስንዴ ኅተራቸው ባዶ ሆኗል።

አብዛኞቹ አገራትም የስንዴ እጥረት በርትቶባቸው፤ በብዙ መቶ ሚሊዮኖች ለሚሆኑ ዜጎቻቸው ዳቦ ለማቅረብ ተቸግረዋል። ይሄን ለተመለከተ የዳቦ ጥያቄ አመጽን በተግባር የተመለከቱባቸውን ግብጽና ሱዳንን በመመልከት‹‹የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል፣ የዳቦ ነገር ጊዜ አይሰጥም›› በሚል እጥረቱ የሕዝብ አመጽን አባብሶ ወደ መንግሥት ግልበጣ ሊያመራ ይችላል በሚል ስጋት ውስጥ ገብተዋል።

ችግሩም ከዩክሬንና ከሩስያ በሚመጣ እህል ላይ ጥገኛ ለሆኑ የአፍሪቃ ሀገራት ራስ ምታት ሆኖ ታይቷል። መረጃዎች እንደሚያመላክቱትም ከሁለቱ አገራት ወደ አፍሪካ ይገባ የነበረውን እህል በአፍሪካ ሀገራት መካከል በሚካሄድ ንግድ ብቻ መተካት የሚቻል አይደለም። ይህም በርካቶችን አስደንግጧል። የቀውሱ ውጤትም በአደባባይ ለመታየት ጊዜ አልፈጀበትም። 90 በመቶ የሚሆነውን የስንዴ ፍላጎቷን ከሁለቱ አገራት በምታስገባው ግብፅ የዳቦ ጋጋሪዎችም የዱቄት ዋጋ በጣም ውድ ሆነብን ሲሉ ተደምጠዋል። ከዩክሬን 60 በመቶ የሚሆነውን የስንዴ ምርት የምታስገባው ሊባኖስም ጭንቅ ውስጥ ናት። አፍ አውጥታ እርጥባን እስከ መጠየቅ ደርሳለች። በዩጋንዳ ተራ የሚባለው ዜጋ ዳቦ መግዛት የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ አገራትም ጊዜያዊ የሚሉትን መፍትሄ በመሞከር ላይ ተጠምደዋል። የዳቦና ስንዴ ውጤቶችን የገበያ ዋጋ ከመተመን አንስቶ ስንዴ ፍለጋ የቀረባቸውን በር እያንኳኩ ናቸው። የስንዴ ምርት ከአገር ውስጥ ፍጆታ ባሻገር ወደ ሌሎች አገሮች እንዳይሸጥ ከልክለዋል። ለዳቦ ስንዴ ዱቄት ድጎማ በጀት መድበዋል።

ምንም እንኳን ሁለቱ አገራት ስንዴ ምርቱን ለመላክ ፈቃደኛ መሆናቸውን ብንሰማም፣ ቀወሱ ግን እንዲህ በቀላል መፍትሄ ያገኛል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ሌላው ቀርቶ የሁለቱም አገራት መሬቶች ሳይታረሱ ፆማቸውን ያደሩ መኖራቸው በሚቀጥለው የምርት ዘመን የሚሰበሰብ ምርት አይኖርም። ይህ ደግሞ የዓለማችንን የምግብ ዋስትና የባሰ ስጋት ውስጥ እንደሚጥለው እርግጥ ነው። ሁኔታውም ስንዴ ከነዳጅ ጋር የሚገዳደር ቀጣይ የዓለማችን ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀብት እንደሚያደርግም የበርካቶች ግምት ነው።

የጦርነቱን መዘዝ ላስተዋለና ውጤቱን ለፈተሸ ኢትዮጵያስ እንዴት ትሆን ይሆን? የሚል የስጋት ጥያቄ መጠየቁ አይቀሬ ነው። እንደሚታወቀው፣ ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ከፍተኛ መጠን ያለው ስንዴ አምራች አገር ነች። ስንዴ ለማምረት ምቹ የሆነ የእርሻ ስነ-ምኅዳር (suitable Agro ecology) እና በስንዴ ዙሪያ የሚመራመሩ የእህል ሳይንቲስቶች እና ልምድ ያላቸው ምሁራን ያላት አገር አላት። ይሁንና ኢትዮጵያ ብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር እያወጣች ስንዴ ከዩክሬንና ሌሎች አገራት ገዝተው ወደ አገር ውስጥ ከሚያስገቡ የአፍሪካ አገሮች አንዷም ናት። ከዓመት ዓመት የሕዝብ ቁጥሯ በእጅጉ እየጨመረ መምጣቱም የአገሪቱ ስንዴን በተለያዩ መንገዶች በስፋት የመጠቀም ፍላጎት እና ምርቱን ለመግዛት የምታወጣውን ወጪ ሰማይ ሰቅሎታል።

የዶክተር ዐቢይ አመራር ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ ታሪክ ለመቀየርም፣ የስንዴ አመራረት ዘዴዋን ለማሻሻል እና የውጭው ዓለም የስንዴ ጠባቂነት ስሜትን በመፋቅ በአገር ቤት ስንዴ በስፋት የሚመረትበትን መንገድ ለመቀየር እየተሠራ ይገኛል። ወደ ሌሎች አማራጮች በመሄድ የመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት መንገድን በመከተል፤ የስንዴ አምራችነትና ተጠቃሚነት አቅምን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ጉዞው ተጀምሯል። በዚህም በከፍተኛ ሥፍራዎች በዝናብ ላይ ተተኩሮ ከሚካሄደው የስንዴ ማምረት ተግባር በተጓዳኝ፤ አገሪቱ ያላትን የውሃ ሀብት በመጠቀም በቆላማ አካባቢዎች በግል ባለሀብቶች ስንዴ በመስኖ እንዲለማ ማድረግ ተጀምሯል።

‹‹Another man's bread will not fill your belly›› የሚል አንድ የአረቦች አባባል አለ። የሌላ ሰው ዳቦ ሆድህን አይሞላልህም ማለት ነው። ኢትዮጵያም ይህ አባባል ጠንቅቆ ገብቷታል። ‹አይመጣምን ትታ፤ ይመጣልን በማሰብ፣ ‹‹የሰው ወርቅ አያደምቅ›› ብላ የራሷን መንገድ ጀምራለች። በስንዴ ምርት የራሷን ፍላጎት ከማሟላት አልፋ ስንዴን ለዓለም አቀፍ ገበያ ለማቅረብ ተጨባጭ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ትገኛለች። ጉዳዩን አስመልክተው ኔሽን ላይ ሀተታ ጽሑፍ ያቀረቡት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ቢልለኔ ስዩም፣ ኢትዮጵያ የስንዴ ፍላጎቷን አሟልታ ስንዴን ለውጭ ገበያ የማቅረብ ውጥኗ የጫወታውን ህግ የሚቀይር ነው›› ማለታቸው የሚታወስ ነው።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የበጋ ስንዴ ልማት የመጀመሪያው ምዕራፍ ብቻ ከ405 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኖ 16 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ማግኘት ተችሏል። በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከ208 ሺህ ሄክታር መሬት 8 ነጥብ 35 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት መሰብሰቡ ከግምት ውስጥ ሲገባ፤ ኢትዮጵያ ስንዴን ኤክስፖርት የማድረግ ውጥን ስኬታማ እንደሚሆን ማረጋገጫ ነው።

በመሆኑም፣ በኢትዮጵያ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ እየተሠራ ያለውን ሥራ ዜጎችን ከዓለም የስንዴ ዋጋ ግሸበት ብቻ ሳይሆን አገርን ከስንዴ ጋር ተያይዞ ከሚመጣ ጫና ማዳን የሚያስችል ነው። ነገሮች እንደታቀዱ በትኩረት ተይዘው ከተጓዙ ደግሞ ለጎረቤት አገራትም እንተርፋለን። እናም ለዚህ ዕቅድና ግብ መሳካት እያንዳንዱ ዜጋ የሚችለውን ሁሉ ማድረግ አለበት።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## ዓባይ...የጋራ ስማችን

**በትረ ሙሴ መልከ (ኢትዮጵ)**

የአማርኛው መዝገበ ቃላት ዓባይን ዋና፣ አባት ሲል ይገልጸዋል። ከዚህ እውነት በመነሳት ዓባይ ማለት ዋና ማለት እንደሆነና አባት ማለት እንደሆነ እንደርስበታለን። ይህ ስም የስሞች ሁሉ በኩር፣ የክብሮች ሁሉ ቁንጮ ነው። ይህ ስም የእኛ ስም ነው። ይህ ስም የኢትዮጵያውያንን ባህልና ታሪክ ተንተርሶ ነፍስ የዘራ ነው። ይህ ስም እትብቱን ከእትብታችን ቀላቅሎ፣ ጥቁርነትን ለብሶ፣ ታሪክና ሥልጣኔዓችንን ተጋርቶ ከጉያችን መንጭቶ የሚፈስ ነው። ታዲያ አባት ቢባል ምን ያንስበታል? ዓባይ ዋናችን ነው፤ ከዚህ ውጪ ምንም ሊሆን ዓይችልም። ለዘመናት በአቅምና በኢኮኖሚ ችግር አባትነቱን ግብጾች ቀምተውን በራሳችን ታሪክ ባይተዋር አድርገውን ነበር። ለዘመናት በእኛ አባትነት ግብጽን ጨምሮ የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ሲያጌጡና ከፍ ሲሉ ነበር። ዘመን ተቀይሮ ይሄኛው ትውልድ በአቅምም በኢኮኖሚም በርትቶ ዓባይን ሊገድብ ሲነሳ ግብጾች አባታችንን አንሰጣችሁም ወልደን ያሳደግነው ልጃችን ነው ሲሉ አመጹብን። አባታችንን ላይሰጡን ብዙ ተሟገቱን፣ ብዙ ዋሹ ይሄ ትውልድ ግን የዋዛ አልነበረምና አባቱን መለሰ..ዓባይንም ገደበ።

እናም ዓባይ የጋራ ስማችን ነው... መታወቂያችን። ኢትዮጵያዊነት የወል ስም ካለው ዓባይ ነው። በብዙ ነገር ተለያይተን በዓባይ ጉዳይ ላይ ግን ዓንድ ነን። ምክንያቱም ዓባይ በጋራ የጻፍነው የጋራ ታሪካችን ስለሆነ። በኢትዮጵያ ምድር እንደ ዓባይ በጋራ ጀምረን በጋራ ልንጨርሳቸው የሚገቡ በርካታ ነገሮች ዓሉ። መለያየት ያበላሻቸው፣ እኔነት ያጸለማቸው በጣም ብዙ ጉዳዮች አሉን። እኚህ ጉዳዮቻችን ተጀምረው እንዲያልቁ፣ ስኬትና ከፍታ፣ እድገትና ስኬት እንዲሆኑን በአንድነት መቆም አለብን። ዓባይ የአንድነታችን ውጤት ነው። ዓለም በተነሳብን ጊዜ፣ ኃያላኖቹ ለግብጽና ሱዳን ወግነው በተነሱብን ጊዜ አንድ ላይ ነበርን። በብዙ ልዩነት ውስጥ አብረን ነበርን። ይሄን ነው የኢትዮጵያዊነት ቀለም የምላችሁ። ይሄን ነው የጋራ ስማችን የምላችሁ። ይሄ አንድነት ዛሬ ላሉብን ችግሮች አስፈላጊ ነው። ዓባይን በጋራ እንደገነባነው ሁሉ በጋራ የምንወጣቸው በርካታ ሀገራዊ እንከኖች አሉብን። አንድነትምን ያክል ኃይል እንደሆነ ዓባይ ምስክራችን ነው። የዓባይ ግድብ፣ የዓባይ ምስጢሩ የአንድነታችን ውጤት ነው።

በዓባይ ጉዳይ ግብጾች ተኝተው አያውቁም። ዛሬም የውሸትና የፖለቲካ ሸሮችን እየጎነጎኑ ተስፋችንን ሊነጥቁን እያሴሩብን ነው። ትውልዱ ግን በአባቱ የማለ፣ በአባቱ ቀልድ የማያውቅ ሆኖ በግብጽና ሱዳም ጩኸት ውስጥ ታሪክ እየሠራ ይገኛል። ይሄ ትውልድ ከእንግዲህ ወደ ኋላ የማይል ነው። ዋናውንና አባቱን ለባዕድ ሰጥቶ በድህነትና በኋላ ቀርነት መኖር አይፈልግም። አይደለም በዓባይ ጉዳይ ወደኋላ ሊል ቀርቶ እነዛ በአቅም ማነስ በግብጾች የበላይነት ያለፉት የአባቶቹ ዘመናት እንኳን የሚያስቆጩት ናቸው። ግብጾች የነጠቁንን አባታችንን ማስመለስ የዚህ ትውልድ የቤት ሥራው ነው። ለዘመናት በአባታችን በዓባይ ግብጽ ስታጌጥ ኖራለች። ከእንግዲህ ዓባይ የእኛ ነው። ካባ ለብሶ፣ ዘውድ ጭኖ ትንሳኤውን ሊያሳየን እነሆ ከአፋፍ ደርሷል። ኢትዮጵያውያን በአንድ ያዜምንለት፣ በአንድ የዘፈንለት ዓባይ ሊሞሸር ዋዜማ ላይ ነው። ጨለማዎቻችን ሊነጉ፣ ተስፋዎቻችን ብርሃን ሊያዩ...ኢትዮጵያ ልትስቅ እነሆ ትንሽ ብቻ ይቀራል።

ዓባይ የገነት መቀነት ነው። ወገቧን ሸብ ያደረገችበት። ገነት ያጌጠችው ዓባይን ተደግፋ፣ ዓባይን ጠምጥማ ነው። ዓባይ የኤዶም ገነት ክንብንብ ነው.. አንገቷ ላይ ጣል ያደረገችው። ዓባይ እምነታችን፣ ጽናታችን፣ የአንድነታችን ክር ነው። ዓባይ ተስፋችን፣ ትንሳኤያችን፣ የከፍታችን ማማ ነው። በዓባይ ግድብ ተስፋን የሰነቁ፣ ነገን አሻቅበው የሚያዩ አያሌ ነፍሶች በኢትዮጵያ ምድር አሉ። እኚህ ነፍሶች እኔና እናተ ነን። እኚህ ነፍሶች መጪው ትውልዶች ናቸው። ከምንበላው ላይ ቀንሰን፣ ከሌለን ላይ ገምሰን ነው ከዘመናት ኩብለላው የመለስነው። ዓባይ በተፈጥሮ ውልደት ከከበቡንና ታሪክና ባህላችንን ከወረሱ እሴቶቻችን አንዱና ዋነኛው ነው። በዚህ ርስታችን ማጌጥ ያለብን እኛ እንጂ ግብጾች ዓይደሉም። ከዚህ ህብስታችን መብላት ያለብን እኛ እንጂ ሱዳኖች አይደሉም። ኢትዮጵያውያን ክፉዎች አይደለንም። እውነትን ሸተው ለተጠጉን ካለን ላይ ማካፈል የለመድን ሕዝቦች ነን። እኛ አብረን እንብላ ስንል ግብጽና ሱዳን ለብቻችን ካልበላን እያሉ ነው። ይሄ ትውልድ ርስቱን አሳልፎ መስጠት አይፈልግም። ከበሉ አብረውን ይብሉ ካልበሉ ግን በርስታችን ላይ የመጠቀም ሙሉ መብት አለን.. ዓባይን ገድበን የመጠቀምና የመልማት መብት።

ሱዳንና ግብጽ የከፉብንን ያክል እኛ ለነሱ ከፍተን አናውቅም። ከትናንት እስከዛሬ አብረን እንልማ፣ አብረን እንደግ እንዳልን ነው። ነገር ግን ወልደው ባሳደጉት የክፋት ሃሳቦቻቸው ከጀመርነው የእድገት ጎዳና ሊያደናቅፉን ብዙ ለፍተዋል አሁንም እየለፉ ነው። በተለይ ዓባይን ለመገደብ በተነሳንበት ሰሞን ከግብጽና ከወዳጆቿ እንዲሁም ከዓለም ዓቀፉ ማሕበረሰብ የደረሰብን ጫና ቀላል የሚባል አልነበረም። አሁንም አልተኙም..የተሳሳተ መረጃዎችን በማሰራጨት፣ በዓባይ ጉዳይ ያለንን አንድነት ለማላላት በርካታ ሴራዎችን በመጎንጎን ላይ ናቸው። እኛ ግን አሁንም በዓባይ ጉዳይ ላይ አልቆምንም.. አልተለያየንም፣ አንድ ላይ ነን። በተለይ የመጀመሪያውን የውሃ ሙሌት በጀመርን ሰሞን፣ በተለይ ሁለተኛውን የውሃ ሙሌት ጀምረን ኃይል ማመንጨት ስንጀምር የሆኑት መሆን እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አልነበረም። አሁንም ሶስተኛውን የውሃ ሙሌት ተከትለው የተሳሳተ መረጃዎችን በማሰራጨትና ከምዕራባውያን ወዳጆቻቸው ጋር እያሴሩብን ነው።

> **ዓባይ እምነታችን፣ ጽናታችን፣ የአንድነታችን ክር ነው። ዓባይ ተስፋችን፣ ትንሳኤያችን፣ የከፍታችን ማማ ነው**

እኛ ግን ያው እንደትናንቱ ነን። የግብጽን የሀሰት ወሬ ችላ ብለን ስለ ዓባይ ጎንበስ ቀና እያልን ነው። እኛና ግብጽ አይሁድንና ክርስቶስን ነን። በዛ በጎለጎታ፤ በርባን ተፈቶ ክርስቶስ ሲሰቀል ብዙዎች ደስ ብሏቸው ነበር። አሁንም የግብጽ ወዳጆች ኢትዮጵያ ከሥራ ግብጽ እንድታተርፍ የሚፈልጉ ናቸው። ይሄ ግን አይሆንም ምክንያቱም ትውልዱ ትንታግ ትውልድ ነው። በዚያ ጊዜ ከአይሁድ ጫጫታ ይልቅ ጲላጦስን ያስፈራው የክርስቶስ ዝምታ ነበር። እኛም የግብጾች ጩኸት ምናችንም ነው። እንደ ክርስቶስ ዝም ብለን በግብጽና ሱዳን ተንኮል ላይ ተረማምደን ትንሳኤያችንን እናያለን። ዓባይ እኮ አባታችን ነው.. እናቱ ደግሞ ኢትዮጵያ ናት። ከአብራኳ ወጥቶ፣ በአብራኳ አድጎ የበለጸገ ልጇ። ታዲያ አባዬ ብለን ብንጠራው ማነው የሚያገባው? ዛሬም ነገም መቼም ዓባይ የእኛ ነው። ለሚወዱን በፍቅር ለተጠጉን እናጋራዋለን። ዓባይን ከመገደብና በዓባይ ላይ ከመጠቀም የሚያግደን ምንም ምድራዊ ኃይል የለም።

አንዳንድ ውሸቶች ሲቆዩ ወደ እውነት ይቀየራሉ። በተለይ ውሸት ፈጣሪ ግለሰቦችና ፖለቲከኞች ሲኖሩ እውነት ክብር ያጣል። የዓባይ ጉዳይ በግብጽ ላይ እንደዚህ ነው። ለዘመናት ያለማንም ከልካይ ተጠቀሙበት ከዛም የእኛ ብቻ ነው፣ የሚመነጨውም ከግብጽ ምድር ነው ሲሉ ማመን ጀመሩ። ማመን ብቻ አይደለም ያላመኑትን ማሳመን ጀመሩ። ትውልዱ እውነትን ሸሮ ዓባይ የግብጻውያን እንደሆነ አምኖ እንዲቀበል ብዙ ለፉ። ለልጆቻቸውም ስለ ዓባይ ውሸት ነገሩ። በዚህ አላበቁም በዓባይ ጉዳይ ላይ የትምህርት ሥርዓት ገንብተው ልጆቻቸውን ስለዓባይ ውሸት ማስተማር ጀመሩ፤ ዓባይ የእኛ ነው ሲሉ። ዓሁን ለግብጻውያን ዓባይ ማለት ከግብጽ የሚመነጭ፣ ለግብጽ ህልውና የተሰጠ አምላካዊ ስጦታ ነው። ይሄ በዘመናት የውሸት አሉባልታ ውስጥ የተፈጠረ እውነት ነው። ዓባይ የኢትዮጵያውያን ነው። ውልደቱ፣ እድገቱ ከሰከላ ማህጸን ነው። ዓሁን ትግላችን በግብጻውያን ልብ ውስጥ የታተመውን የውሸት እውነት ፍቆ ከተቻለ ዓባይ የግላችን እንደሆነ ማሳየት ካልተቻለ ደግሞ ዓባይን በጋራ እንድንጠቀመው ማድረግ ነው።

በግብጽ ምድር ለዓባይ የተዘፈነውን ያክል ለማንም አልተዘፈነም። ዛሬም ድረስ የጉዳያቸው አንደኛ ነው። ብሄራዊ ክብራቸው፣ ታሪካዊ ህልውናቸው አድርገውት ለዘመናት ኖረዋል። ይሄ የውሸት ትርክት በዚህ በእኔና በእናንተ ተሸሮ ዓባይ የእኛ ነው ስንል ተነስተናል። ትግላችንም ፍሬ አፍርቶ እየገደብነው እንገኛለን። ከመገደብም አልፈን ሶስተኛውን የውሃ ሙሌት በማጠናቀቅ ላይ ነን። የሚቀረን በአንድነት የገነባንውን፣ በአንድነት የደከምንለትን የህዳሴ ግድባችንን እልል ብሎ መመረቅ ነው። የሚቀረን በጋራ ትንሳኤዓያችንን ማጣጣም ነው። የሚቀረን እንደ ህዳሴ ዓይነት ሌሎች ግድቦችን መሥራት ነው። በነገራችን ላይ ግብጻውያን ዓባይን የህልውናቸው መሰረት ያደረጉበትን ብዙ ማስረጃዎችን ማየት እንችላለን። ግብጽ ውስጥ በዓባይ የሚምሉ አሉ። ግብጽ በየዓመቱ ከአምስት ሺ በላይ የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ታስመርቃለች በጣም የሚገርመው ደግሞ እኚህ ሁሉ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፋቸውን የሚሠሩት በዓባይ ወንዝ ላይ መሆኑ ነው። ግብጽ ውስጥ ዓባይ ለብዙ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ ሃሳብ ነው። ይሄ ማለት ግብጾች በዓባይ ዙሪያ ምን ያክል ርቀት እንደተራመዱ የሚያሳይ ነው። አሁን ጊዜው የእኛና የዓባይ ነው። በዓባይ ላይ የግብጽ የበላይነት አክትሟል። ዓባይ ወደ እናቱ ተመልሷል።

በየትኛውም መስፈርት ቢታይ የኢትዮጵያ ግድብ መሥራት ግብጽና ሱዳንን አይጎዳም ይጠቅማቸዋል እንጂ። ግን ውስጣቸው ያስቀመጡት የኔነትና የብቻ ሃሳብ ስላለ ዓባይን መጋራት አይፈልጉም። ይሄ ሃሳብ ምን ያክል እውነት እንደሆነ ለማየት ጥቂት ምሳሌዎችን ላስቀምጥ። ካቻምና የመጀመሪያ የውሃ ሙሌት ስናከናውን ካጠቃላዩ የውሃ ይዘት 4 ፐርሰንት ብቻ ነበር የተጠቀምነው። ቀጥለን በዓመቱ አምና ማለት ነው 13 ፐርሰንት ብቻ ነው ለሙሌት የተጠቀምነው ይሄ ማለት በመጀመሪያው ሙሌት 96 ፐርሰንቱ በሁለተኛው ሙሌት ደግሞ 87 ፐርሰንቱ ውሃ ወደ ግብጽና ሱዳን ፈሷል ማለት ነው። ከዚህ እውነት በመነሳት የውሃ እጥረት ይፈጠራል፣ ተፋሰስ ሀገራት ይራባሉ የሚሉት የግብጽና የሱዳን አሉባልታ ውሸት መሆኑን እንደርስበታለን። ምንም አይደለም የግብጽና ሱዳን ስጋት የኢትዮጵያን ብልጽግና ከመፍራት የመነጨ ነው። ኢትዮጵያን ከመፍራት፣ ብልጽግናዋን ከመስጋት የመነጨ የበታችነት ስሜት ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከህዳሴ ግድባችንና ከዚህ በኋላም በምትገነባቸው ግድቦች የምታገኘው የኃይል፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የሥልጣኔ፣ የዘመናዊነት ጸጋ ስጋት ሆኗቸው ነው ዛሬ ላይ ይሄን ሁሉ ችግር እየፈጠሩ ያሉት።

የሶስተኛውን የውሃ ሙሌት ተከትሎ እንኳን የተለያዩ የውሸት ዜናዎች ከግብጽ ሚዲያ እየተሰሙ ነው። አንድ ጋጤጠኛ በራሱ የዩቲዩብ ገጽ ላይ ግድቡ እየተሰነጣጠቀ ነው፤ ሕዝቡ አሁን ላይ ስለ ህዳሴ ግድብ ማሰብ አቁሟል የሚል ከእውነት ውጪ የሆነ የሀሰት ወሬዎችን ሲያራግብ ነበር። ከሰሞኑ ግብጽ ስለ ህዳሴው ግድብ የሚመለከታቸውን ሀገራት ጋብዛ በህዳሴው ዙሪያ እየተወያየች ነው። እውነቱ እኛጋ ነው ያለው። የህዳሴ ግድባችን ከሃሳባችን ያልወጣ፣ ከሃሳባችን የማይወጣ የህልውናችን ማህተም ነው። ጠላት ያው ጠላት ነው ጥሩ ነገር አያወራም። ገና ከዚህ በኋላም የተለያዩ የውሸት ወሬዎችን እንሰማለን። ከእኛ የሚጠበቀው እንደ ክርስቶስ ዝም ብለን እየሠራን ወደ ትንሳኤያችን መጓዝ ነው። ዓባይ አባታችን ነው፤ የሚያስቆመን ማንም የለም። የግብጾች ህልውና እንደመሆኑ እኛም ህልውና ነው። በዓባይ ግድብ ላይ መቶ ሃያ ሚሊዮን ድሃ ሕዝቦች ተስፋን ቋጥረዋል። እምነትን ጥለዋል። በዓባይ ግድብ ላይ መጪው ትውልድ ኩራትና ብኩርናን በዛሬዎቹ እኛ ላይ ጥሏል። ታዲያ ዓባይ እህል ውሃችን ቢሆን ምን ይገርማል?

# ‹‹የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ ባህል እየሆነ መጥቷል››

**- አቶ አስፋው ተክሌ**
**የሕብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር**

**አስቴር ኤልያስ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሕብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኢኮኖሚያዊውንም ሆነ ማሕበራዊውን ችግር ከመፍታት በተጨማሪ ማሕበራዊ ትስስርን በማጠናከሩ ረገድ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ስለመሆኑ ይነገራል። ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ አዲስ ዘመን ከኮሚሽኑ ኮሚሽነር አስፋው ተክሌ ጋር ቆይታ አድርጎ እንደሚከተለው አጠናቅሯል።

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ የበጎ አገልግሎት ስራ ብሎ የሰያቸው ስራዎች የትኞቹ ናቸው? ምን ምንስ እያከናወነ ይገኛል?**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** በዚህ ዓመት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራ ብለን ወደስራ የገባነው ሰባት መርሃግብሮችን ይዘን ነው። የመጀመሪያው በሰብዓዊና ማሕበራዊ አገልግሎቶች ላይ የሚከናወን ሲሆን፣ ይህም ቤት እድሳትና ማዕድ ማጋራትን ታሳቢ ያደረገ ስራ ነው። ሁለተኛው አረንጓዴ ልማትና አካባቢ ጥበቃ ሲሆን፣ በተለይ ከግሪን ሌጋሲና ከተማ ከማጽዳት ጋር ተያይዞ የሚሰራ ነው። በዚህ መርሃግብር ከአንድ ሚሊዮን በላይ ፈቃደኞችን ለማሳተፍ እየሰራን እንገኛለን። ሶስተኛው የጤና መርሃግብር ሲሆን፣ በዚህም በአዲስ አበባ ላይ ከ20 ሺ. ባለይ የሚሆኑ ነዋሪዎች የአይን፣ የጥርስና ጠቅላላ የህክምና አገልግሎት በነጻ እንዲያገኙ በተለያዩ የመንግሥት ሆስፒታሎች ውስጥ እንዲሁም የግል ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች ውስጥ ያሉ ተቋማት እንዲሰጡ አቅደን ወደስራ ገብተናል።

ሌላውና አራተኛው ደግሞ የደም ልገሳ መርሃግብር ሲሆን፣ በዚህ ደግሞ ከ35 ሺ. ዩኒት በላይ ደም እንዲለገስ በአዲስ አበባ እየሰራን ነው። አምስተኛው መርሃግብር የማጠናከሪያ ትምህርት ሲሆን፣ የማጠናከሪያ ትምህርቱን በ 134 ትምህርት ቤቶች ላይ አቅደን ከሁለት ሺ. በላይ በጎ ፈቃደኛ መምህራንን በመመዝገብ እየሰራን ያለ ስራ ነው። የመንገድ ትራፊክ ደግሞ አምስተኛ መርሃግብራችን ሲሆን፣ መንገድ ትራፊክ ላይ በከተማችን ውስጥ ከ 130 በላይ አደባባዮች አሉ፤ እነዚህን ለይተን በክረምቱ በጎፈቃደኞች በማሳተፍ ለማሰራት ነው ያሰብነው።

ስድስተኛው ወሰን ተሻጋሪ በጎ ፈቃድ አገልግሎት መርሃግብር ነው። ይህ ከአዲስ አበባም አልፈን በሌሎች ክልሎች ላይ ወንድማማችነትና አብሮነትን ይበልጥ ለማጠናከር የምንሰራበት ነው። ሰባተኛውና የመጨረሻው መርሃግብር የተለያዩ የንቅናቄና የግንዛቤ መርሃግብር ብለን የያዝነው ‹ኑ! የመጽሐፍ መደርደሪያውን እንሙላው› በሚል የአብርኆት ቤተ መጽሐፍ እና ሌሎች በከተማው የሚገኙ ቤተ መጻሕፍትን ለማሟላት የተጀመረ ስራ ነው። ከልዩ ልዩ ሱስ ጋር ተያይዞም በተለይ ወጣቶች ለሱስ ተጋላጭ እንዳይሆኑ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን እየሰራን በጠቀስኳቸው ሰባት ዋና ዋና መርሃ ግብሮች ላይ አቅደን እየሰራን እንገኛለን።

የዚህ ዓመት የበጎ ፈቃ አገልግሎት እንደከዚህ በፊቱ የሶስት ወር ብቻ ሳይሆን ሰፋ በማድረግ የአምስት ወር የክረምት በጎ ፈቃ አገልግሎት ብለን ከግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምረናል፤ እስከ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በሰባቱም መርሃግብሮች ላይ እንደከተማችን ለማከናወን ወደ ተጨባጭ ስራ ገብተናል።በዚህም ትልልቅ ውጤቶች እያገኘንበት እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- በእስካሁኑ እንቅስቃሴያችሁ ምን ውጤት ማስመዝገብ ችላችኋል?**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** በሰባቱም መርሃግብር ላይ ስራ የተጀመረ ሲሆን፣ የተሳካም ስራ እየሰራን ነው። ለአብነት ያህል የመጀመሪያውን የሰብዓዊና የማሕበራዊ አገልግሎትን ብንወስድ ባሳለፍነው አምስት ወር ውስጥ በአዲስ አበባ ላይ ከሶስት ሺ.400 የአጋውያውያን፣ የአቅመ ደካሞችን እንዲሁም የአገር ባለውለታዎችን ቤት እናደሳለን ብለን አስበን፤ ከዚህ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ሶስት ሺ. 88 ቤት አካባቢ ጨርሰናል። ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ቤት በአዲስ መልክ ተሰርቶ የተጠናቀቀ ነው።በዚህ ተግባር ብቻ ከ15ሺ. አራትመቶ አርባ በላይ አባወራዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ አለ። በአጠቃላይ እዚህ ላይ በእያንዳንዱ ተግባር ላይ ከ702 ሚሊዮን ብር በላይ ሀብት አሰባስበን አንድ ቤት በአማካይ እስከ 400 ሺ. ነው ሙሉ እድሳት እየተደረገለት ይገኛል። በእርግጥ የቤቱ ካሬ የሚወስነው ሲሆን፣ ከፍ ሲል እስከ 700 ሺ. ብር ዝቅ ሲል ደግሞ እስከ 300 ሺ. ብር ድረስ ይሆናል። በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በከተማችን ደረጃ በመጀመሪያው መርሃግብር ላይ ሶስት ሺ. 88 ቤት እስካለፈው ሳምንት ድረስ አጠናቀናል። ከእነዚህ ቤቶች አብዛኛዎቹ ለተጠቃሚ የተላለፉ ናቸው። ለተጠቃሚዎች ስናስተላልፍ የቤት እቃ እንኳ ሶፋን የመሳሰለ፣ አንዳንድ ቦታ ለይ ደግሞ ቴሌቪዥንም ጭምር በማካተት ሲሆን፣ ቤቱን ያደሱ ተቋማት እቃውንም ጭምር የሚያሟሉበት ሁኔታ አለ።

በአብዛኛው የታደሱ ቤቶችን ስናስተውል አንዳንድ ቦታ አፍርሰን የሠራነው መንደር ነው ማለት ይቻላል። አንድ አካባቢ ላይ እስከ ሃያና ሰላሳ ቤት ድረስ አፍርሰን እያደስን ነው። ይህ ሲሆን ደሳሳ ጎጆዎችን እየቀየርን፣ ሕጻናት የሚጫወቱበትን ቦታ እየሠራን፣ የጋራ መታጠቢያ ስፍራን እንዲሁም የጋራ መጻዳጃ ቤት እያዘጋጀንም ጭምር ነው። እንዳንድ ቦታ ላይ ትንሽ በቂ ቦታ ስናገኝ ለአንዳንድ ማሕበራዊ አገልግሎቶች ለምሳሌ ለሰርግ፣ ለለቅሶ እንዲሁም በዓላትንም ሲያከብሩ ሊገለገሉበት የሚችሉ እድልም እየፈጠርን ነው። ከዚህም የተነሳ በዚህ መርሃ ግብር በጣም የተሳካ ስራ ሰርተናል።

ሁለተኛው የማዕድ ማጋራት መርሐግብር ነው። በዚህ አምስት ወራት ውስጥ የማዕድ ማጋራቱ በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል። ከመስከረም አንድ ጀምሮ መስቀልንመ ጨምሮ የሚከበር በዓል እንዳለ ሁሉ የኢሬቻ በዓል ሥነሥርዓትን ለማክበር ዝግጁዎች ነን፤ በተለይ ለበዓሉ የሚመጡ ወንድም እህቶቻችን (የኦሮሚያ ክልል ዝግጅት እንዳለ ሆኖ) በዓሉ የሁላችን ስለሆነ እኛም የእንኳን ደህና መጣችሁ መርሃግብር እናዘጋጃለን። በማዕድ ማጋራት በተለይ እንደ አገር አሁን ያለንበት ሁኔታ ይታወቃል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም የዋጋ ንረቱ እጅግ የበረታ ሆኗል። ለዋጋ ንረቱ መባባስ በተለይ በምስራቅ አውሮፓ ላይ ያለው ጦርነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የፈጠረው ተጽዕኖ አለ። እንደ አዲስአበባ የተለዩ ወደ 378 ሺ. በሁሉም ክፍለ ከተማ ላይ መደገፍ ያለባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ለይተን እስካሁን ወደ አራት መቶ ሰባት ሺ. አካባቢ የሕ ብረተሰብ ክፍል ማዕድ አጋርተናል። ያጋራናቸው ማዕድ የራሱ የሆነ ደረጃ ወጥቶለት ከሶስት እስከ አምስት ሊትር ዘይት፣ ከ15 እስከ 25 ኪሎ ጤፍ፣ አምስት ኪሎ ሩዝ፣ አምስት ኪሎ ማካሮኒ፣ አምስት ኪሎ ፓስታ ሲሆን፣ በመሃል ደግሞ ለነበሩ ለፋሲካ እና ለረመዳን በበዓላት የሚያስፈልጉ እንደ ዶሮና እንቁላል የመሳሰሉ ነገሮችን አሟልተናል። በተጨማሪም በሁሉም ክፍለከተሞች የእስልምናውንም ሆነ የክርስትና እምነት ተከታዩ ዘንድ ሄደን የእንኳን አደረሳችሁ መልካም ምኞት ገልጸናል። በማዕድ ማጋራቱም የተሳካ ስራ ሰርተናል።

በአረንጓዴ ልማትና አካባቢ ጥበቃ አንጻር ኢትዮጵያ ተነሳሽነቱን ወስዳ የግሪን ሌጋሲውን ለማሳካት ባለፉት ሶስት ዓመታት የተሰሩ ስራዎች ይታወቃሉ። አራተኛውም እንዲሳካ በአዲስ አበባ ደረጃ ውጤታማ ስራ ተሰርቷል። እዚህ ላይ ከጉድጓድ ቁፋሮ አንጻር ወደ ሰባት ሚሊዮን 999 ሺ. 416 ጉድጓድ በበጎ ፈቃደኛ ብቻ አንድም ወጪ ሳይወጣበት የተቆፈረ ነው። ይህን በጎ ስራ የሰሩ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ተማሪዎች፣ የመንግሥት ሰራተኞች፣ ኤምባሲዎች፣ የኃይማኖት ተቋማትና የተለያዩ አካላት በሰፊው የተሳተፉበት ስራ ሲሆን፣ ወደ ስምንት ሚሊዮን አካባቢ በሚጠጋ ጉድጓድ ችግኝ መትከል ችለናል። እንደከተማው ወደ 13 ሚሊዮን አካባቢ ችግኝ ለመትል እየተሰራ ነው።

አሁንም እንደ አዲስ አበባ የአንድ ጀምበር የችግኝ ተከላ በቀጣዮቹ ሳምንታት ውስጥ ይካሄዳል፤ ከአራት ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል እዚህ ላይ የአዲስ አበባ በጎ ፈቃደኛና የተለያየ የሕብረተሰብ ክፍልም ተረባርቦ የ 13 ሚሊዮኑን የአዲስ አበባ እቅድ ለማሳካት እየተንቀሳቀስን ነው።

በዚህ መርሐግብር ስር ያለው ሌላው ቦይ የማጽዳት ስራ ነው። አዲስ አበባ ከፍታ ላይ እንደመሆኗ ለጎርፍ የተጋለጠች ከተማ ነች። የመሰረተ ልማቱ ችግር ሆነው እዚህም እዚያም የሚታዩትን ነገሮች ትልልቅ በጀት የሚፈልጉ ስራዎች እንዳሉ ሆነው ቦይ የማጽዳት ለምሳሌ እዚህም እዚያም ቦይ እየተደፈነ የተለያየ አደጋ እንዳይደርስ ሕብረተሰቡን እያሳተፍን እንገኛለን። ይህ በሰፊው ሕብረተሰቡ በተለይ ቅዳሜ ቅዳሜ ባህል አድርጎ በየቦታው እየተሳተፈበት የሚገኝ ነው።



**በአብዛኛው የታደሱ ቤቶችን ስናስተውል አንዳንድ ቦታ አፍርሰን የሠራነው መንደር ነው ማለት ይቻላል። አንድ አካባቢ ላይ እስከ ሃያና ሰላሳ ቤት ድረስ አፍርሰን እያደስን ነው፡፡ይህ ሲሆን ደሳሳ ጎጆዎችን እየቀየርን፣ ሕጻናት የሚጫወቱበትን ቦታ እየሠራን፣ የጋራ መታጠቢያ ስፍራን እንዲሁም የጋራ መጸዳጃ ቤት እያዘጋጀንም ጭምር ነው**

ከጤና አንጻር ሃያ ሺ. የሚሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የአይን፣ የጥርስና ጠቅላላ ምርመራ በከተማችን ውስጥ ያሉ የአይንና የጥርስ ሕክምና ክሊኒኮች የግልን ጨምሮ እዚህ አግልግሎት ላይ በሰፊው እንዲሳተፉ እርገናል። እስካሁንም ሁለት ሺ. 578 የሚሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ነጻ ሕክምና ተጠቃሚ ሆነዋል። በመርሃግብሩም 216 በጎ ፈቃደኛ ዶክተሮች እተሳተፉበት ነው። ይህን አገልግሎት በተለያየ ጤና ተቋማት ውስጥ እየሰጠን እንገኛለን። በተጨማሪነት ከሚቀጥሉት ሳምንታት በኋላ ለሴቶች በተለየ ሁኔታ የነጻ የማሕጸን ጫፍ ካንሰር ቅድመ ካንሰር ሕክምና ከአሁን ሳምንት ጀምሮ እናስጀምራለን። ሁለተኛው ደም ልገሳ ሲሀን፣ እዚህ ላይ 35 ሺ. ዩኒት የሚጠጋ ደም ለማስለገስ እቅድ ይዘን ተንቀሳቅሰናል፤ በአሁኑ ወቅት ዘጠኝ ሺ. 187 ዩኒት ደም ማስለገስ ችለናል። አራተኛው መርሃግብራችን የማጠናከሪያ ትምህርት ነው። በዚህም የማጠናከሪያ ትምህርት 32 ሺ. 516 ተማሪዎች እየተማሩ ነው። ከአንድ ሺ. 500 በላይ በጎ ፈቃደኞችን መምህራን እንዲያስተምሩ ለመመዝገብ አስበን እስካሁን አንድ ሺ. 315 መምህራን በነጻ የበጎ አገልግሎት ማስተማሩ ላይ በመሳተፍ ላይ ናቸው። እዚህ አካባቢ ያለን አቅድ ወደ አንድ መቶ ሺ ለመድረስ ነው። ነገር ግን መደበኛ ትምህርቱ የተጠናቀቀው ሐምሌ አምስት አካባቢ በመሆኑ የማጠናከሪያ ትምህርቱን ዘግየት ብለን እንድንጀምር አድርጎናል። በአሁኑ ሰዓት ግን የምዝገባ ስራው ወደ 46 ሺ. አካባቢ ደርሷል። በመሆኑም ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ ያሰብነውን እቀድ ለማሳካት እየተጓዝን ነው። በእርግጥ ካቀድነው እቅድ አንጻር በአሁኑ ሰዓት 50 በመቶ ደርሰናል። ትራፊክን በተመለከተ ስድስት ሺ. በጎ ፈቃደኞችን በ130 አደባባይ ላይ እያሳተፍን እንገኛል። በአሁኑ ሰዓት ከስድስት ሺ. መካከል 3 ሺ. 971 በጎ ፈቃደኞች በ130 አደባባዮች ላይ የደንብ ልብሱን ለብሰው የትራፊክ ፍሰቱን እንዲሁም ሕብረተሰቡን የማስተባበር ስራ በሁሉም አደባባዮች ላይ እያሳለጡ ይገኛሉ።

ሌላው መርሐግብራችን ወሰን ተሻጋሪ ነው፤ ወሰን ተሻጋሪ እስካሁን ከአዲስ አበባ እና ፊንፊኔ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ወደ ሁለት ሶስት ከተሞች ላይ ችግኝ እየተከልን ነው። ለጋጣፎ ላይ ተክለናል። ገላን፣ ሰበታ እንዲሁም ቡራዩ ላይ በተመሳሳይ ችግኝ ተክለናል።

በዚህ መርሐግብራችን የአዲስ አበባ ወጣቶች ሁሉም ወደአገሪቱ ክልል ሄደው ችግኝ የመትከል፣ አካባቢን የማጽዳት፣ የደም ልገሳ እና ሌሎች የበጎ ፈቃድ ስራ ላይ ለመሳተፍ ከአንድ ሺ. 200 በላይ ወጣቶችን በሁሉም የአገራችን ክልሎች ሄደው አገልግሎት እንዲሰጡ እቅድ ይዘን እየሰራን ነው። በአጠቃላይ በአዲስ አበባ ዙሪያ ባሉ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከተሞች ላይ አገልግሎቱን እየሰጠን ነው። ከሌሎች ንቅናቄ አንጻር እስካሁን ‹‹ኑ! የመጽሐፍ መደርደሪያውን እንሙላ›› በሚል መርህ እንደተቋማችን ብቻ ከሶስት ሺ. 900 መጻሕፍት አሰባስበን ለአብርሆት ቤተ መጽሐፍት አስገብተናል። እንዲሁም በማረሚያ ቤት ውስጥ ያሉ ወጣቶችም የተለያዩ ሥልጠናዎች ብሎም

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድረግ መጻሕፍቱን የማሰባሰብ ስራ ላይ በሰፊው እየሄድን ነው።

የጸረ ሱስ ንቅናቄ በተለይ ወጣቱ ለሱስ ተጋላጭ እንዳይሆን በማሰብ እስካሁን በሶስት ክፍለ ከተማ ላይ ከወጣቶች ጋር ውይይት አካሂደናል። ከ14 ሺ በላይ ወጣቶችም የግንዛቤ መድረክ እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል። በአጠቃላይ እንደ ከተማ በዚህ አምስት ወራት ውስጥ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን በላይ ብር የመንግሥት ወጪን ለማዳን አቅደን እየሰራን ነው። አሁን በመርሃግብራችን ከያዝነው ደግሞ በከተማ ደረጃ በክብርት ከንቲባዋ የሚመራ በልዩ ትኩረት በፕሮጀክት እየተሰሩ ያሉ ተግባራትም አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ተግባራቱ ምን ምንድን ናቸው?**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** ከበጎ ፈቃድ ጋር የሚያያዙ በክብርት ከንቲባዋ በተለየ ሁኔታ እየተመሩ የሚሰሩ ሶስት ስራዎች አሉ፤ አንዱ የቤት እድሳት ሲሆን፣ ሁለተኛው በከተማችን ደረጃ እየተሰሩ ያሉ የዳቦ ፋብሪካዎች ናቸው። ሶስተኛ ደግሞ ሸገር ዳቦ መሸጫዎች ሲሆኑ፣ እነርሱም እየተሰሩ ነው። ከቤት እድሳት አንጻር እንደ ከተማ አስተዳደራችን ሞዴል አምስት ክፍለ ከተሞች ተለይተው ለሰው ተኮር ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው። በዚህም በክብርት ከንቲባ እንዲሁም በምክትል ከንቲባ፣ በስራ አስኪጁና በከንቲባ ከፍተኛ አማካሪ ፕሮጀክቶች ከስድስት መቶ 66 በላይ ቤቶች ከባለ አራት ወለል እስከ ባለ ዘጠኝ ወለል ሕናጻዎች እየተሰሩ አቅመ ደካሞችና በጣም የተለየ ድጋፍ የሚፈልጉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ቤቱ ተጠናቆ እንዲገቡበት እየተደረገ ነው። በዚህም ከ761 ሚሊዮን ብር በላይ የባለሀብቶች ሀብት ተሰባስቦ ቤቶቹ እየተጠናቀቁ ይገኛሉ። እነዚህ ቤቶች በተለይም ቂርቆስ፣ ልደታ፣ ነፋስ ስልክ፣ የካ በተለየ ሁኔታ አስተባባሪ ኮሚቴው እየደገፈ ይገኛል። በቀሩት ክፍለ ከተሞች ላይም በተመሳሳይ ቤቶች እየተሰሩ ነው። ይህ ከያዝነው ከበጎ ፈቃድ መርሃግብራችን ውጪ ነው።

ሌላው የዳቦ ፋብሪካ ነው፤ አዲስ አበባ ውስጥ በባለሀብቶችና በሕብረተሰቡ ተሳትፎ ወደ 32 አካባቢ ዳቦ ፋብሪካ ደርሰናል። ልደታ ላይ ብቻ ወደ ዘጠኝ፣ ነፋስ ስልክ አምስት፣ የካ አምስት፣ አዲስ ከተማ ሶስት፣ ቂርቆስ አንድ፣ ቦሌ ሶስት፣ ለሚ ኩራ ሶስት አካባቢ እንዲሁም ቃሊቲ ላይ ሶስት የዳቦ ፋብሪካ ሲሆን፣ ይህም በገንዘብ ሲተመን ከ 887 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን ሀብት ባለሀብቶች፣ የተለያዩ ተቋማት ፋብሪካውን እየገነቡ ነው፤ ይህም የኑሮ ውድነቱ በሕብረተሰባችን ላይ የተለየ ጫና እንዳያሳድር እየተሰራ ያለ ስራ ነው። እንዲሁም የሸገር ዳቦ መሸጫ ሱቆች ላይ ዳቦም፣ አትክልትም መሸጫ እንዲሁም የካፌ አገልግሎት መስጫ ሆኖ እንዲያገለግል ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው። ይህ ስራ በባለሀብቶችና በሕብረተሰብ ተሳትፎ ለሕብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጥ 74 አካባቢ የሚሆን ዳቦ መሸጫዎችን መስራት ተችሏል። ኮልፌ፣ የካ፣ ልደታ፣ ነፋስ ስልክ፣ ቂርቆስ፣ ቦሌ፣ አቃቂ ቃሊቲ ላይ እየተሰራ ይገኛል። ይህም በገንዘብ ቢተመን ከ 250 ሚሊዮን ብር በላይ ሀብት የፈሰሰበት ነው።

ሌላው የምገባ ማዕከል ነው። በከተማችን ወደ ሰባት አካባቢ በዚህ በክረምት ወቅት በቀን አንድ ጊዜ እንኳ መመገብ የማይችሉ በየጎዳናው ላይ ያሉ አረጋውያንን በመሰብሰብ አገልግሎቱን እንዲያገኙ የሚደረግበት ቦታ ነው። ቢያንስ አንድ ማዕከል ላይ ብቻ ከ 3 ሺ እስከ 3 ሺ 500 የሚስተናገዱበት ትልልቅ የምገባ ማዕከላት እየተሰሩ ነው። ልደታ፣ የካ፣ አዲስ ከተማ፣ ቂርቆስና ቦሌ ላይ ተገንብተው አገልግሎት እየተሰጠ ነው። በእነዚህ አራቱ ተግባራትም ከበጎ ፈቃድ ስራ ጋር በጎ ፈቃደኞች የሚሳተፉበት እንደመሆኑ መጠን በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ የመንግሥት ወጪ ወደ ሶስት ቢሊዮን ብር አካባቢ ማዳን ችለናል። በተለይም በልዩ ትኩረት በፕሮጀክት እየተሰሩ ያሉ ተግባራት ከፍተኛ ወጪ እና መዋዕለ ንዋይ ፈስሶባቸው እየተሰሩ ነው፤ እነዚህ ለብቻቸው በክብርት ከንቲባዋ የሚመራ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ወጥቶበታል። እንደተቋማችን ደግሞ አስቀድሜ በጠቀስኳቸው ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት ማፍሰስ ተችሏል።

በክረምት የበጎ ፈቃድ ስራችን አንድ ሚሊዮን 500 ሺ የሕብረተሰብ ክፍል ማሳተፍ መቻል አለብን ብለን አቅደን እየሰራን ነው። እስካሁን ወደ 816 ሺ ሰዎች እየተሳተፉ ነው። በአረንጓዴ አሻራ ብቻ ከ790 ሺ በላይ ሰዎች ጉድጓድ በመቆፈር እንዲሁም ችግኝ በመትከል በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የበጎ አገልግሎት ሰጪው የግንዛቤ ደረጃ እንዴት ይገለጻል?**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** በዋናነት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ የሕዝቡ ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ነው። አዲስ አበባ ላይ ከካቻምናው የአምናው በጣም ከፍተኛ



**የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ ባህል እየሆነ መጥቷል። ልክ ክረምት ሲመጣ የበጎ ፈቃ አገልግሎት ላይ አሳትፉን በሚል ወደ ተቋማችንም ወደ ክፍለከተሞችም የሚሄድ ሰው ቁጥር እየጨመረ ይገኛል**

ቁጥር ነው። ለምሳሌ አምና ወደ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የሕብረተሰብ ክፍል በበጎ ፈቃድ ስራ ላይ ባወጣናቸው መርሐግብሮች ላይ ተሳትፏል። በጣም እጅግ ከመጨመሩ የተነሳ በዚህች አምስት ወር ብቻ አምና ዓመቱን ሙሉ ስንሰራ ከነበረው ስራ በላይ በጎ ፈቃደኞችን ለማሳተፍ አስበን ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ነው በአምስቱ ወር ያሰባሰብነው፤ እስካሁን 816 ሺ የሚሆኑ በጎ ፈቃደኞች እየተሳተፉ ነው። በቀጣይ ቀናት ውስጥ በተለያዩ መርሃግብሮች ላይ የያዝነውን እቅድ እናሳካለን ብለን እናስባለን። በዚህ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ከፍተኛውን ተሳትፎ እያደረገ ያለው ወጣቱ ነው። በተለይ ከትምርት ቤት የተመለሱ ወጣቶች በአካባቢያቸው የጸጥታ ስራ ላይ ሚናቸውን እየተወጡ ይገኛሉ። በጓድጓድ ቁፋሮም ሆነ በችግኝ ተከላው ላይ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሳተፈ ያለው ወጣቱ ነው። የትራፊክ ፍሰቱ እንዲሳለጥ ከማድረግም አኳያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት የበጎ ፈቃ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ከዚህ ጎን ለጎንም ባለሀብቱም ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ ባህል እየሆነ መጥቷል። ልክ ክረምት ሲመጣ የበጎ ፈቃ አገልግሎት ላይ አሳትፉን በሚል ወደ ተቋማችንም ወደ ክፍለከተሞችም የሚሄድ ሰው ቁጥር እየጨመረ ይገኛል። ከመንግሥት ሰራተኛው በተለይ መምህራን በክረምቱ ወቅት እረፍት እንደመሆናቸው አሳትፉን የሚል ተነሳሽነት አላቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ያጋጠማችሁስ ችግር ምን አይነት ነው፤ እንዴትስ ተወጣችሁት?**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** የበጎ ፈቃደኛው ቁጥር በጣም እየጨመረ ነው፤ ይህን እንደችግር አናየውም። አንድ እያጋጠመን ያለው ችግር ግን እንደሚታወቀው አዲስ አበባ ውስጥ አቅመ ደካማና ደሃ የሕብረተሰብ ክፍሎች አሉ። በከተማችን የቤት ችግር ደግሞ በጣም ፈተና የሆነበት ጊዜ ነው። ቤቶችን በከፍተኛ ደረጃ እያደስን ስንመጣ አብዛኛዎቹ የሚታደሱ ቤቶች ማደስ የሚባሉ ሳይሆን አፍርሰን እየሰራን ነው በሚያስብል ደረጃ እያደስን ነው። ጭቃ ቤቶችን በብሎኬት እየቀየርንና መጸዳጃ ቤቶች እንዲኖራቸው እያደረግን ነው። አብዛኛው ቦታ ላይ ደግሞ የቤት ቁሳቁስንም ጭምር እያሟላን ነው፤ በዚህ ጉዳይ የተለያዩ ተቋማትን እየጠየቅን እየተባበሩንም ጭምር ይገኛሉ። ቤት አይገንቡ እንጂ ሶፋ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች እምስት አስር ሃምሳ ድረስ ሶፋዎችን እየሰጡን ነው።

በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ሰው በስፋት እየተሳተፈ በመሆኑ ለእኔ ይሰራልኝ ጥያቄ በዝቷል። አዲስ አበባ ውስጥ ከ150 ሺ በላይ የቀበሌ ቤቶች አሉ። እነዚህ ሁሉ በአንድ ጊዜ ይታደስልኝ የማለታቸው ጉዳይ አቅማችንን እየፈተነው ነው። አቅማችንን ያላገናዘበ ግፊት በየቦታው እየታየ ነው። ይሁንና ሕብረተሰቡን እያስገነዘብነው በመጣን ጊዜ በጣም የከፋ ድህነት ውስጥ ያለው እከሌ ነውና ከእኔ ይልቅ ለእርሱ ስሩ የሚሉ እንዳሉ ሁሉ የእኔ ቀድሞ መሰራት አለበት የሚሉም አልታጡም። ይህ በእርግጥ በጣም የከፋ ፈተና ባይሆንም ሕብረተሰቡ ግን እኛ የከፋ ችግር ውስጥ ያለውን እንደምናስቀድም መገንዘብ መቻል አለበት። እኛ ቤቱን ስንሰራ በጣም የከፋ የሚለውን በአራት መስፈርት አውጥተን ነው፤ ከአራተኛው ይልቅ በአንደኛ ደረጃ የከፋ ሁኔታ ውስጥ ላለው ቅድሚያ የሚሰጠው ይሆናል፤ ይሁንና ለምሳሌ በአንድ ክፍለ ከተማ አራተኛ ደረጃ ላይ የከፋ ሁኔታ ውስጥ ላለ ሰው ሊሰራለት ይችላል፤ ምክንያቱም አንደኛ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ የከፋ ሁኔታ ውስጥ ያለ ሰው ላይኖር ይችላልና ነው። ሌላው ክፍለ ከተማ ደግሞ አንደኛ ደረጃ ላይ የከፋ ሁኔታ ውስጥ ያለ አካል እያለ አራተኛ ደረጃ ላይ ላለው አይሰራለትምና ይህ ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል። አንዳንድ ቦታ ለእኔ አልተሰራም በሚል እንደሙብት ገፍቶ የሚመጣበት ሁኔታ እየታየ ስለሆነ ነው።

በዚህ አጋጣሚ የእናንተን ተቋም ጨምሮ ሚዲያውን በከፍተኛ ሁኔታ ላመሰግን እወዳለሁ። ምክንያቱም የበጎ ፈቃድ ስራ ባህል እንዲሆን ከፍ ያለ ሚና ተጫውታችኋልና። በአንድ ቦታ ላይ የተሻለ ስራን ለሌላው ተሞክሮ ይሁን ዘንድም መግለጽ ሚናው ቀላል የማይባል ነው። እንዲሁም ሚዲያው መተባበሩና ወንድማማችነቱ እንዲጎለብት በማድረጉ በኩል የድርሻውን እየተወጣ ነው። በመሆኑም ማመስገን እፈልጋለሁ።

ከዚህ ባለፈ ግን እኛ መረጃውን ሳናደርሳቸውም ቀርተን ሊሆን ይችላል፤ ተቋማት በበጎ ፈቃድ ሥራው በብዛት እየተሳተፉ አይደለም። በተቻለ መጠን አዲስ አበባ ውስጥ እስከ ባለ ዘጠኝ ወለል ሕንጻዎችን አንድም የመንግሥት ገንዘብ ሳይገባበት በራሳቸው ኮንትራክተር ቀጥረው እየገነቡ ያሉትና ለድሃው እየሰሩ ያሉ ባለሀብቶችና ተቋማት ያሉትን ያህል ሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ከመሳተፍ አንጻር ውስንነቶች አሉ። ሁሌም የእኛ መርህ በጎ ፈቃደኝነትን ከተፈጥሮ ሕግ ጋር ነው አስተሳስረን የምንሄደው። ለምሳሌ አበባ ውበቱ ለሰው ነው፤ ውሃ መልሶ ራሱ አይጠጣም። ስለሆነም እኛ በጎ ያደረግንለት አካል ምንኛ እንደሚረካ በማሰብ በተቻለን ሁሉ በጎ ለማድረግ ብንጥር መልካም ነው እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በጎ የተደረገለት የሕብረተሰብ ክፍል ግብረ መልስ እና የበጎ አድራጊው እርካታ ምን ይመስላል?**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** በጎ እየተደረገለት ያለ የሕብረተሰብ ክፍል ከፍተኛ ደስታ ውስጥ ነው ያለው። በተለይ ቤት የሚታደስላቸው እንዲሁም በማዕድ መርሃግብሩ የሚሳተፉ ግብረ መልሳቸው መልካም ነው። ይህ ሰው ተኮር ተግባር በትክክል እየተሰራ መሆኑን አመላካችም ነው። መንግሥት ላይ ያላቸው አመኔታም እየጨመረ መጥቷል። መንግሥት ችግሬን ይፈታልኛል ብለው በማመናቸውም አገር ለመጥቀም ያላቸው ተነሳሽነት ጨምሮ አይተናል። በአሁኑ ወቅት ሕብረተሰቡ መንግሥትን እያደመጠ ነው። እንዲሁም በእርስ በእርሱም እየተደማመጠ ነው። ለምሳሌ እኛ ቤት አድሰን ስንሰጣቸው የአካባቢው ሰው ደግሞ ቡና አፍልቶና ዳቦ ጋግሮ እርስ በእርስ የመደጋገፉን ሁኔታ እያሳየ ነው። ከዚህ የተነሳ የመረዳዳት ባህላችን እየተጠናከረ ነው። ሰው ደግሞ በዚህ ሒደት በጣም ደስተኛ እየሆነ ነው።

ሌላው ከበጎ አድራጊዎች መካከል እየተሰሩ ያሉ ስራዎች አሉ፤ ለአብነት ያህል የካ ክፍለ ከተማ ላይ የዶክተር እመቤት የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ ለሕብረተሰቡ በጣም ብዙ ስራዎችን ሰርቷል። ለምሳሌ በሕክምና መርሃግብራችን ነጻ የጥርስ ሕክምና አገልግሎት ወደ 500 ለሚጠጉ ሰዎች መስጠት ጀምሯል። በተጨማሪ ሌሎች የቀበሌ ቤቶችን ዶክተሯ አድሰው እየሰጡ ነው፤ ለወጣቱ ደግሞ መዋያ ሜዳ ስታድየም እየተሰራ ነው። በዚህም ባለሀብቱ የሚያገኘውን ሀብት ለራሱ ብቻ መጠቀም ሳይሆን ማሕበራዊ ኃላፊነቱን ከሚጠበቀው በላይ እየተወጣ ይገኛል። በመሆኑም ትልልቅ ተቋማት በተግባሩ ላይ በዚህ መልኩ እየተሳተፉ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የበጎ ፈቃድ ስራ ሲባል ወደሰዎች አዕምሮ የሚመጣው የክረምት ስራ ተደርጎ ነው፤ ከተጠቀሱት ሰባት መርሃግብሮች ቀጣይነት ያላቸው የትኞቹ ናቸው?**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** ከማጠናከሪያ ትምህርት ውጪ ሁሉም መርሃግብሮች በበጋውም ቀጣይ ናቸው። በበጋ መደበኛ ትምህርት ስለሚጀመር የማጠናከሪያ ትምህርት ጎን ለጎን ማካሄድ አይቻልም። ከዚህ ውጭ ሰብዓዊና ማሕበራዊ መርሃግብራችንን በበጋውም እንቀጥላለን። ቤት ማደሱን እንቀጥላለን፤ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም የእውቅና እና የምስጋና መርሃግብር እናካሂድና ቀጣይ እንዳርገዋለን። የዓመቱ እቅዳችን 3 ሺ 400 ብቻ አይደለም፤ ምንያቱም 3 ሺ 400 በአምስት ወር ብቻ ለመስራት ያሰብነው ነው። የዓመቱ እቅዳችን ከአምስት ሺ ቤት በላይ ለመስራት ነው።

አረንጓዴ ልማት ላይ በጋ ላይ ችግኝ አንተክልም፤ ነገር ግን የተተከሉ ችግኞችን እንንከባከባለን። በተጨማሪ አካባቢን ማጽዳት በቀጣይነትም የምንሰራው ስራ ነው። የጤና መርሃግብራችንም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚቀጥል ይሆናል። ወሰን ተሻጋሪ ስራም ቀጣይ የሚሆን ሲሆን፣ ለምሳሌ አዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች ዘንድ በመሄድ እህል እናጭዳለን፤ እንዲሁም ተጨማሪ አገልግሎቶችንም የምንሰጥ ይሆናል።

የትራፊክ አገልግሎቱ ላይ በአሁኑ ወቅት በ130 አደባባዮች እየሰራን ነው፤ በጋ ላይ ይህን የአደባባይ ቁጥር እንቀንሳለን። ትኩረት የምናደርገውም በጣም የትራፊክ መጨናነቅ አለባቸው በምንላቸው ላይ ይሆናል። ማዕድ ማጋራቱም ቀጣይ የሚሆን ሲሆን፣ በእርግጥ በዚህ ላይ የምንሰራው የተመጽዋችነት ስሜት እንዳይፈጠር በማድረግ ነው። እየተጠናቀቀ ባለው ዓመትም በአዲስ አበባ ከስድስት ሺ ብር በታች የወር ደመወዝ ያላቸውን የመንግሥት ሰራተኞች በማዕድ ማጋራቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርገናል። ማለትም 77 ሺ የሚጠጉ የመንግሥት ሰራተኞች ተጠቃሚ ሆነዋል፤ በተለይ የጸጥታ ጥበቃ ላይ የሚሳተፉ በጣም አነስተኛ የወር ደመወዝ ያላቸውን ፖሊሶች ታሳቢ አድርገናል። ድጋፉም በአማካይ ከሶስት ሺ በላይ የሚጠጋ ዱቄት፣ ዘይትና መሰል ድጋፍ ተደርጎላቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ኮሚሽነር አስፋው፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የግብርናውን ምርታማነት በአግሮ - ኢንዱስትሪ ፓርኮች የማሳደግ ጥረት

**አንተነህ ቸሬ**

መንግሥት መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ብሎ ትኩረት ከሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት አንዱ ነው። ፓርኮቹ የወጪ ምርቶችን በማምረት የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት፣ የገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት፣ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የሕብረተሰብ ክፍል የስራ እድል በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብስብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሰረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም ሰፊ የሰው ሃይልና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል።

በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ ዘርፍ መናኸሪያ እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ እንዲሁም ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤቶች ተገኝተውበታል። በተለይም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድሎችን በመፍጠር ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

በተለይም የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የታየባቸው የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአርሶ አደሮች የግብይት ሰንሰለቱን ቀላል በማድረግ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ። ባለሀብቶች የግብርና ግብዓቶችን ከአርሶ አደሮች እንዲቀበሉ በማድረግ አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ያህል እንዲጠቀሙ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ።

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን፣ አዳሚ ቱሉ ወረዳ የሚገኘው የ‹‹ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ›› በሀገሪቱ ከተገነቡ የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች (Integrated Agro-Industry Parks) መካከል አንዱ ነው። ፓርኩ በሚያዝያ ወር 2013 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ነው የተመረቀው። የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የወተት፣ የማር፣ የስጋና የእንቁላል ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አምራቾች የሚሰማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ነው። ፓርኩ በሙሉ አቅሙ ወደ ስራ ሲገባ ለ100ሺ ዜጎች የስራ እድል ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በፓርኩ ምርቃ ወቅት ‹‹ግብርናችንን በአግሮ ኢንዱስትሪዎች ልማት የበለጠ እናዘምነዋለን። ዛሬ የተመረቀው የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለግብርናው ዘርፍ፣ ለአርሶ አደሮቻችን እና ለሸማቾች የኢትዮጵያን የብልጽግና ራዕይ የሚያሳይ ነው›› ብለው ነበር።

ምንም እንኳ የፓርኩ አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም 86 በመቶ ቢሆንም፣ አሁን ባለሀብቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚችልበት አቅም ላይ ደርሷል። ፓርኩ ባለሀብቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ባከናወናቸው ተግባራት አንዳንድ አምራች ኩባንያዎችም ወደ ፓርኩ ገብተው በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችሏቸውን የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ። አንዳንድ አምራች ድርጅቶች ደግሞ የሙከራ ምርት መጀመራቸው ተገልጿል።

ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተው እንዲሰሩ የፓርኩን ገፅታና አቅም ለባለሀብቶች የማስተዋወቅ መርሃ ግብር ሰሞኑን በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በመርሃ ግብሩ ከተሳተፉ



ፓርኩ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ለ100ሺ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል

ባለሀብቶችና የግል አልሚዎች መካከል 42 የሚሆኑት ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደ ፓርኩ ለመግባት ቃል ገብተዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ተጨባጭ ለውጥ እንዲያስመዘግብ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ምርታማነት ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ የዘርፉን እድገት ለማጎልበት የኦሮሚያ ክልል የግሉ ዘርፍ በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ በስፋት እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር፣ የአርሶ አደር ኢንቨስትመንትን የማጠናከር፣ የወጣቶችን ተሳፎና ተጠቃሚነት የማሳደግ እና የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማስፋፋት ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ጠቁመዋል። በነዚህ ተግባራትም ብዙ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው ወደ ስራ መግባታቸውን፣ ከስምንት ሺ በላይ አርሶ አደሮች ከሊዝ ነፃ መሬት ወስደው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ መሰማራታቸውን እንዲሁም በበርካታ ማሕበራት የተደራጁ ጀማሪ ባለሀብቶች ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉን ገልጸዋል።

‹‹አሁን ምቹ ሁኔታ ስለተፈጠረ ኢንቨስት አድርጉ። ከዚህ በላይ ምቹ ሁኔታ ሊፈጠር አይችልም፤ ከዚህ የተሻለውን ምቹ ሁኔታ የምትፈጥሩት እናንተ ናችሁ። የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ዝግጅቱን አጠናቆ እናንተን እየጠበቀ ይገኛል›› በማለት ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ገብተው በአግሮ-ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ ጥሪ አቅርበዋል። የክልሉ መንግሥት የመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦትን ጨምሮ የኢንቨስትመንት ስምሪትን ቀላልና ፈጣን የሚያደርጉ አሰራሮችን ተግባራዊ እንደሚያደርግም አስታውቀዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በበኩላቸው እንዳሉት፤ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ሀገራዊ ፋይዳቸው ከግምት ውስጥ ገብቶና ሰፊ ጥናት ተደርጎባቸው ከተቋቋሙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል አንዱ ነው። ፓርኩ የመሰረተ ልማት ግንባታውና አቅርቦቱ በተሻለ ደረጃ ተሟልቶለታል።

መንግሥት አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በመገንባት የወጪ ንግድን ከመጨመር፣ የሥራ እድልን ከመፍጠር፣ የአርሶ አደሮችን ተጠቃሚነት ከማሳደግና የባለሀብቶችን ተወዳዳሪነት ከማጎልበት አኳያ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸው በመሆናቸው ባለሀብቶች መንግሥት የፈጠረውን ምቹ እድል እንዲጠቀሙና ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ተግባራት ላይ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል።

አቶ መላኩ ባለሀብቶች ወደ አግሮ ኢንዱትሪ ፓርኮች እንዲገቡ በመንግሥት የሚበረታታቱበትን ምክንያት ሲያስረዱ፣ ‹‹በሀገሪቱ የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች እያጋጠሟቸው ካሉ ችግሮች መካከል አንዱ የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር ነው። አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ግን የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር የተፈታላቸው ማምረቻዎች ናቸው። ‹‹የምርት ግብዓቶችን ከውጭ ማምጣት ስለማያስፈልግ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ሲሰማሩ የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር አያጋጥማቸውም።›› ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ቀላል ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙ በመሆናቸው ቴክኖሎጂውን ለማስተዳደርና በቴክኖሎጂውም የሰው ኃይል ለማግኘት ተመራጭ ናቸው። የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን ሕይወት ለመቀየርም የተሻለ እድል ይፈጥራሉ።

የመሰረተ ልማት አቅርቦት እንዲሁም የመንግሥት ክትትልና ድጋፍ ማነስ የአምራች ዘርፉ ችግሮች እንደሆኑ ይታወቃል ያሉት ሚኒስትሩ፣ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ግን የመሰረተ ልማት አቅርቦትንም ሆነ የክትትልና ድጋፍ ተግባራትን በተቀላጠፈ ሁኔታ ማግኘት የሚያስችሉ መሆናቸውን አስታውቀዋል። ‹‹እነዚህ ሁኔታዎች ወደ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገቡ ባለሀብቶች ችግሮቻቸው ቢያንስ በከፊል የተፈቱላቸው እንደሆኑ ያሳያሉ። ስለሆነም ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብቶ መስራት ለባለሀብቶች የተሻለ እድል ይፈጥራል›› በማለት ገልጸዋል።

አብዛኞቹ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተጠናቀቁበት ጊዜና የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ የተከሰተበት ጊዜ በመገጣጠማቸው የውጭ ባለሀብቶች በሚፈለገው ልክ ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ መሰማራት አልቻሉም ያሉት አቶ መላኩ፣ መንግሥት በፈጠረው ምቹ ሁኔታ ምክንያት በቀጣይ ጊዜያት የውጭ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ውስጥ ሲሰማሩ ውድድሩ ሊከብድ እንደሚችልና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች ተጠቅመው ወደ ፓርኮቹ ገብተው ማልማት እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል።

‹‹በአግሮ-ኢንዱስትሪ ስራዎች ላይ ለመሰማራት የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግሮች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝባቸው ብዙዎቹ ምርቶች ጥሬ ምርቶች ናቸው፤ ከውጭ የሚገቡት ምርቶችም ከሀገር ውስጥ ለውጭ ገበያ ቀርበው እሴት የተጨመረባቸው ምርቶች ናቸው። ስለሆነም ይህን ክፍተት ማስተካከል ያስፈልጋል። አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ይህን አለመመጣጠን በማስተካከል ገቢ ምርቶችን ለመተካት ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል›› ብለዋል።

‹‹በአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው ለማልማት ፍላጎት ካሳዩ 94 ባለሀብቶች መካከል ስድስቱ ማልማት ጀምረዋል። ከስድስቱ መካከል ደግሞ ሦስቱ ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ መላክ ጀምረዋል። በሁለት ዓመታት ውስጥም ከ 16 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ችለዋል። ባለሀብቶቹ ከ 144ሺ ባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ጋር የምርት ትስስር ፈጥረዋል። በነዚህ የኢንቨስትመንት ተግባራት ከተፈጠረው የሥራ እድል እና ከተገኘው የውጭ ምንዛሬ በተጨማሪ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ምቹ ገበያ ለመፍጠር እንዲሁም ለተሻለ የአርሶ አደሮች ምርታማነትና ተጠቃሚነት ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይህም የአግሮ-ኢንዱትሪ ፓርኮች ለኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት እድገት የላቀ ሚና እንዳላቸው አመላካች ነው›› ሲሉ ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛውን የውጭ ምንዛሬ የምታገኘው ከግብርና ምርቶች እንደሆነና አብዛኞቹ ምርቶች እሴት ሳይጨመርባቸው ለገበያ እንደሚቀርቡ የጠቀሱት አቶ መላኩ፤ በምርቶቹ ላይ እሴት ጨምሮ ለገበያ በማቅረብ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማሳደግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግርን ለማሳካት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው የተናገሩት አቶ መላኩ፤ ሽግግሩ በመንግሥት ጥረት ብቻ የሚሳካ እንዳልሆነም ነው ያመለከቱት። ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በማልማት የምጣኔ ሀብት ሽግግር እቅዱን እውን ማድረግ እንደሚገባ አስረድተዋል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙ ባለሀብቶች በበኩላቸው የኢንቨስትመንት ስራቸውን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ የሚችሉ አሰራሮች እንዲዘረጉላቸውና ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶች እንዲቃለሉላቸው ጠይቀዋል። የኢንቨስትመንት ስራዎችና የሰላም መስፈን ቀጥተኛ ግንኙት እንዳላቸውም ጠቅሰው፣ አስተማማኝ ሰላምን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ መንግሥት አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለመገንባት እስካሁን ድረስ 25 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ወጪ አድርጓል። ይህ ወጪ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ውስጥ ገብተው በምርት ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የተደረገ ነው።

‹‹መንግሥት ይህን ያህል ገንዘብ ያወጣው በዋናነት ለመሰረተ ልማት ግንባታዎች ነው። ይህም መንግሥት የባለሀብቶችን ወጪ መጋራቱን ያመለክታል። መንግሥት የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ባያከናውን ኖሮ ባለሀብቶች መሰረተ ልማቶችን አሟልተው እንዲገቡ ያስገድድ ነበር።›› ያሉት አቶ መላኩ፣ ‹‹የኢንቨስትመንት ስምሪትን ቀላል ለማድረግ ከ10 በላይ የሚሆኑ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተግባራት በኦንላይን አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገም ነው›› ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ተሾመ አዱኛ እንዳሉት፤ በኦሮሚያ ክልል ለግብርና ልማት የሚውል በቂ መሬት እንዲሁም የምርት ዓይነቶች ቢኖሩም ይህን አቅም ለመጠቀም የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎች ሳይፈጠሩ በመቆየታቸው ባለፉት ዓመታት ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ መገኘት የነበረበት ውጤትና ጥቅም ሳይገኝ ቀርቷል።

ከለውጡ ወዲህ፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት፣ በግብርናው ዘርፍ ውጤት የተገኘባቸው በርካታ ለውጦች መመዝገባቸውን የቢሮ ሃላፊው ጠቁመው፤ ግንባታው ተጠናቆ ወደ ስራ የገባው የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ የግብርናውን ዘርፍ አቅም በመጠቀም ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚደረገው ጥረት አካል እንደሆነም ተናግረዋል። ኢንዱስትሪ ፓርኩ በውስጡ የሚሰማሩ ባለሀብቶችና የኢንቨስትመንት ስራዎቻቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ደረጃውን ጠብቆ እንደተገነባም ገልጸዋል።

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም። ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል።

የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው። ስለሆነም መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል። ይህም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን እንደ ኤሌክትሪክ ያሉ መሰረተ ልማቶችን፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# ሕወሓት - የኢትዮጵያ ‹‹ሪቪዥኒስት››

ሙሉቀን ታደገ

> **ሕወሓት አገሪቱን በሚያስተዳድርበት ዘመን ሲከተለው የነበረው የመንግሥት አወቃቀር የፌዴራላዊ መንግሥት ነበር። ይሁን እንጂ የሕወሓት መንግሥት አምባገነናዊ ስለነበር የብሔር ብሔረሰቦችን መብት አንድም ቀን ሲያከብር አልታየም። በመሆኑም በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ሕዝቦች ሕወሓትን «አይንህ ላፈር» ብለው ከመንበረ ስልጣኑ አውርደውና አዋርደው እንዳባረሩት የምናስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው**

ሪቪዥኒስት (Revisionist) የሚለው ቃል ከማርክሲዝም ፍልስፍና የተገኘ ነው። በማርክሲዝም ፍልስፍና ሪቪዥኒስት (Revisionist) ማለት ደግሞ ከዚህ በፊት የነበረን ማንነት እና የኑሮ ፍልስፍና በአዲስ አመለካከቶች እና አካሄዶች በመበረዝ አንድ ማህበረ ሰብእ (ማኅበረሰብ) ለዘመናት ይዞት የቆየውን አመለካከት ማጉድፍ ወይም ማበላሸት እንደማለት ነው።

ወያኔም ከኢትዮጵያውያን ታሪክ እና ፍላጎት ተቃርኖ የሆኑ አዲስ የማታለያ ቃላቶችን በመደርደር ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ይዘውት የኖሩትን ተባብሮ እና ተከባብሮ የመኖር የጋራ እሴቶች ክፉኛ በርዟል። በዚህም ኢትዮጵያውያን በጥርጣሬ እርስ በእርስ እንዲተያዩ ከማድረጉም ባለፈ በቋንቋ ተቧድነው እርስ በርስ እንዲበላሉ አድርጓል። በመሆኑም እኔ ወያኔን የኢትዮጵያ ሪቪዥኒስት (Revisionist) ብዬዋለሁ።

ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ይዘዋቸው የቆዩትን ተባብሮ እና ተከባብሮ የመኖር የጋራ እሴቶች በመበረዝ ለመከፋፈል እና ለመበታተን ከተጠቀመባቸው በመርዝ የተለወሱ ቃላቶች መካከል ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የተሰኙት በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሾች ናቸው።

ወያኔ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተጠቀመው ኢትዮጵያውያንን በብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በተሰኙ ጽንሰ ሃሳቦችን እንደ ዋነኛ መሣሪያ ተጠቅሞ በመከፋፈል ነው። ወያኔ ብሔር ብሔረሰቦች የተሰኙ ቃላትን ከምዕራባውያን ምንም ሳያላምጥ ይብላው እንጂ ብሔር፤ ብሔረሰቦች የሚለውን ቃል ትርጓሜ አንድም ቀን ተገንዝቦት የሚያውቅ አይመስልም። ለማወናበጃነት ከመጠቀሙ በስተቀር።

እንደሚታወቀው ብሔር ብሔረሰቦች የተሰኙ ቃላት እያደጉ እና እየዳበሩ የመጡት በአውሮፓ ፊውዳላዊ አስተዳደር ወድቆ የኢምፔሪያሊዝም አገዛዝ መምጣቱን ተከትሎ ስለመሆኑ በርካታ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች በተለያዩ ጥናቶቻቸው አመላክተዋል።

«ሃፍረት እና ይሉኝታ» የማያውቀው ወያኔ ግን ብሔር እና ብሔረሰብ የሚባሉትን እሳቤዎች እራሱ እንደፈጣረቸው በማስመሰል እና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መብት ከወያኔ ህልውና ጋር የተያያዘ በማስመሰል ለዘመናት በአገራችን ተገንብቶ የነረውን ማንነታችን በምዕራባውያን የቅጥፈት ሸቀጥ ሸጦ በላ።

ወያኔ ብሔር ብሔረሰቦች የሚለውን ጽነሰ ሃሳብ ከእነማርክስ እንደመውሰዱ መጥን ከማርክሲዝም ፍልስፍና አንጻር አንድን ማህበረ ሰብእ ብሔር ለሚያስብሉት የሚችሉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? የሚለውን ነጥቦች መመልከት ተገቢ ይመስለኛል። ብሔር ማለት በዘር ወይም በጎሳ ላይ የተመሰረተ ማህበረሰብ ማለት አይደለም። በማርክሲዝስ ፍልስፍና ብሔር ማለት በጎሳ ሳይሆን በታሪክ የተቀናጀ ማህበረሰብ ማለት ነው። ይህ የመጀመሪያው አንድን ማህበረ ሰብእ ብሔር ሊያስብለው የሚችል መስፈርት እንጂ አንድ ማህበረ ሰብዕ በታሪክ ለረጅም ዘመናት ስለተቀናጀ ብቻ ብሔር አይባልም ሊባል እንደማይችል ያትታል።

ስለሆነም አንድ ማህበረ ሰብእ ብሔር ሊያስብለው የሚችለው ሁለተኛው መስፈርት ደግሞ አንድ ዓይነት ቋንቋ መናገር ሲችል ነው። ይህ ማለት ግን የተለያዩ ማህበረ ሰብእ ሆነው አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ የሉም ማለት አይደለም። ለምሳሌ አሜሪካ እና እንግሊዝ የተለያዩ ማህበረ ሰብእ ናቸው። ነገር ግን የሚናገሩት ቋንቋ አንድ ዓይነት ነው፤ እንግሊዝኛ። ይሁን እንጂ የተለያዩ ማህበረሰቦች አንድ ዓይነት ቋንቋ ስለተናገሩ ብቻ አንድ ብሔር ናቸው ማለት ግን አይደለም። ስለዚህ የተለያዩ ማህበረሰቦች በታሪክ ስለተቀራረቡ እና አንድ ዓይነት ቋንቋ ስለተናገሩም ብቻ ተመሳሳይ ብሔር ናቸው ሊባሉ አይችሉም። ስለሆነም ከታሪካዊ ቁርኝት እና ዓይነት ቋንቋ ከመናገር ባለፈ ማህበረሰቦቹ የተሳሰረ ኢኮኖሚ ሊኖራቸው እንደሚገባ ማርክሲዝም ያስገነዝባል። አለበለዚያ እንደ አንድ ብሔር ሊቆጠሩ አይችሉም። ስለዚህ በአንድ ማህበረሰብ መካከል የሚኖር የኢኮኖሚ ትስስር አንድን ማህበረሰብ ብሔር እንዲባል ከሚያስችሉ መስፈርቶች አንዱ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ሌላኛው እና አራተኛው አንድን ማህበረ ሰብእ ብሔር ሊያስብል ከሚችሉ መስፈርቶች መካከል በማህበረሰቡ መካከል የሚታይ ተመሳሳይ የሆነ የሥነ - ልቦናዊ ዘይቤ (psychological makeup ) ነው።

አምስተኛው መስፈርት እና አንድን ማህበረሰብ ብሔር ሊያሰኘው ከሚችሉ መመዘኛዎች መካከል ደግሞ አንድ ማህበረሰብ ራሱን የቻለ ሉአላዊ ግዛት ሲኖረው ነው። እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ሊባል ይገባል። ይህም ምንድን ነው? ወያኔ ኢትዮጵያውያንን በብሔር ሲከፋፍል ብሔር መያዝ የሚገባውን መስፈርት ለማሟላት ሲል ብቻ በኢትዮጵያ አዲስ የግዛት አስተዳደር መሠረተ። በዚህም እስካሁን ድረስ በከፍተኛ ደረጃ በኢትዮጵያውያን መካከል መቃቃር እና መጣላትን ፈጥሮ እንመለከተዋል። በዚህም በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ሳይቀር ውዝግብ ተፈጥሮ እንመለከታለን።

ስድስተኛው መስፈር እና አንድ ማህበረ ሰብእ ብሔር ሊያሰኝ ከሚችሉ መመዘኛዎች መካከል የሚታይ ባህል የሚለው ይገኝበታል። ከዚህ አንጻር ወያኔ እንደ አንድ ብሔር መድቦ ያስቀመጣቸው ብሔሮች የተለያየ ባህል ሲተግብሩ መታየታቸው ነው።

ከስድስቱ መስፈርቶች አንዱ ከጎደለ አንድ ማህበረ ሰብእ አንድ ብሔር እንደማይቆጠር የሃሳቡ ጠማቂዎች እነማርክስ አጥብቀው ያስተምራሉ። ወያኔ ግን ኢትዮጵያውያንን ለመከፋፈል ስለፈለገ ብቻ የተለያዩ ጎሳዎች የሚገኙባቸውን ግዛቶች እንደ አንድ ብሔር እየቆጠረ ይጨፈልቃል። በዚህም ግማሹን በሽሮ ግማሹን በዶሮ የሆነ ተግባርን እየተገበረ አገራችን ላይ በቃላት ለመግለጽ የሚከብዱ በደሎችን ሲፈጽም ኖሯል።

ሪቪዥኒስቱ (Revisionist) ሕወሓት ኢትዮጵያውያንን ለመነጣጠል የተጠቀመው ሌላው ፌዴራሊዝም የሚለውን የመንግሥት አወቃቀር (state structure /forms of government) በመንግሥት ዓይነቶች (types of government) ተክቶ ለመስራት የሄደበት እርቀት ነው። ይህ የወያኔ አደገኛ አካሄድ መሆኑን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊገነዘበው ይገባል ባይ ነኝ።

ወያኔ በእነዚህ የምዕራባውያን የመከፋፈያ ቃላት በማታለል ኢትዮጵያውያንን ከሰውነት ዘር አውርዶ በብሔር ስር እንዲወሸቁ አድርጓል። ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀርን መንግሥት ዓይነቶች (types of government) በመተካት ኢትዮጵያውያንን አጭበርብሯል። እዚህ ላይ ሁሉም ሰው እንዲገነዘብልኝ የምፈለግው ነገር የፌዴራላዊ አወቃቀርን ሥርዓት በአገራችን መዘርጋቱ የምደግፍ እንጂ የምቃወም አለመሆኑን ነው። ነገር ግን ሕወሓት የሄደበትን የመንግሥት ዓይነቶች (types of government) በመንግሥት አወቃቀር (state structure /forms of government) በመተካት ፌዴራሊዝምን ከፍትህ ጋር ለማቆራኘት የሄደበት አግባብ እጅጉን አደገኛ ነው። የፌዴራሊዝም ሥርዓት በአገራችን ከተዘረጋ ፍትህን በፈለገውነው ልክ ማስፍን እንደሚቻል እያስመሰሉ ሕዝብን ማታለል ተገቢነት የለውም።

ወድ ኢትዮጵያውያን ድፍረት አይሁንብኝና አንድ እንድትገነዘቡልኝ የምፈለገው ነገር አለ። መንግሥትን በተለያዩ መመዘኛዎች ልንከፋፍለው አንችላለን። አንደኛው በዓይነቱ (types of government ) ነው። ከዚህ አንጻር ዴሞክራሲያዊ፣ ወታደራዊ አምባገነናዊ፣ ንጉሣዊ፣ ኦሊጋርኪ፣ አስረስቶክራሲ ፣ ወዘተ ብለን ልንከፋፍል እንችላለን። ከእነዚህ የመንግሥት ዓይነቶች ተነስተን ስንመለከት ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እስካለ ድረስ የፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ባይከተልም እንኳን የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መብት በተለይም በራስ ቋንቋ የመማር ፣ የመዳኘት ወዘተ መብቶች ያለምንም እና ያለማንም ከልካይነት እንደምንተነፍሰው አየር በነጻነት ልናገኘው እንድምንችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሌላው እና ሁለተኛው መንግሥትን ለመመደብ ከምጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ አወቃቀር (state structure /forms of government) ነው። ከዚህ አንጻር መንግሥትን አሀዳዊ ፣ ፌዴራላዊ እና ኮንፌዴራላዊ ብለን እንከፍላለን። ይህ አካሄድ የመንግሥት ስልጣን በየትኛው አካል መያዝ አለበት የሚለውን ሁነኛ ጉዳይ ለመወሰን የሚረዳን ይሆናል። ነገር ግን አንድ ብሔር ወይም ጎሳ በራሱ ቋንቋ የመማር ፣ የመዳኘት ወዘተ መብቶችን ያለምንም እና ያለማንም ከልካይነት ሊያጎናጽፍ ይችላል።

አንድ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ሳይሆን ፌዴራላዊ ስለሆነ ብቻ ፍትህን ማስፈን አይችልም። ፌዴራላዊ ስለሆነ ብቻ አንድ ጎሳ በራሱ ቋንቋ የመማር፣ የመዳኘት ወዘተ መብቶች ያለምን እና ያለማንም ከልካይነት ያስከብራል ማለት አይደለም። እነኝህ የብሔር ብሔረሰቦች መብቶች ሊከበሩ የሚችሉት አገሪቱን የሚያስተዳደርው መንግሥት ዴሞክራሲዊ እና ዴሞክራሲያዊ ሲሆን ብቻ ነው።

ለዚህ አንድ ቀላል ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። ወያኔ አገር በሚመራበት ወቅት ይከተለው የነበረው የመንግሥት አወቃቀር ፌዴራላዊ ነበር። ነገር ግን ፌዴራላዊ መንግሥት ስለሆነ የዜጎችን መብት ማስጠብቅ አልቻለም። ከዚህ አንጻር በዚህም ፌዴራሊዝም የመንግሥት አወቃቀር መሆኑን በመደበቅ እና ሕዝብን በማታለል ፍትህን ለማስፈር ሁነኛ ማሳያ አድርጎ መውሰድ ትክክል አለመሆኑን እንገነዘባለን።

ይህንን ስል በምክንያት እንጂ እንዲሁ በግብዝነት ስላለመሆኑ አንድ መሳያ ማንሳት ያስፈልጋል። እንደሚታወቀው ሕወሓት አገሪቱን በሚያስተዳደርበት ዘመን የሚከተለው የመንግሥት አወቃቀር የፌዴራላዊ መንግሥት ነበር። ይሁን እንጂ የሕወሓት መንግሥት አምባገነናዊ ስለነበር የብሔር ብሔረሰቦችን መብት አንድም ቀን ሲያከበር አልታየም። በመሆኑም በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ሕዝቦች ሕወሓትን አይን ላፈር ብለው ከመንበረ ስልጣኑ አውርደው እንዳባረሩት የምናስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው ።

ሌላው ሕወሓት በብሔር ብሔረሰቦች የፈጠረው ነገር ቢኖር ትምክተኝነትን (chauvinism) ነው። በዚህም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ጎሳዎች የራሳውን ጎሳ ከፍ እያደረጉ የሌላውን ዝቅ በማድረግ ወደ አላስፈላጊ ግጭት እንዲገቡ ያሰለጥናል! በገንዘብም ይረዳል። በዚህም በርካታ አሸባሪውን ሸኔን ጭምሮ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጣላቶች በነጻ እንዲሸጡ በማድረግ የግብጽን ተልእኮ ይዘው አገራችንን እያተራመሱ ይገኛሉ።

በመጨረሻም የሪቪዥኒስቱን (Revisionist) ወያኔ አስተሳሰቦች ሀገር አፍራሽ መሆናቸውን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገንዘቦ ወደ ቅድሞ ማንነቱ ለመመለስ ጠንክሮ መሥራት አለበት! መልዕክቴ ነው።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ንባብ ብፌዎች

ተገኝ ብሩ







በመዲናችን ትልልቅ አውደ ርዕዮችን የሚያስተናግደው ኤግዚቢሽን ማዕከል በሰዎች ተሞልቷል። በተከፋፈሉ የድንኳን መጠለያዎች ውስጥ የተለያዩ መጽሐፍት በአይነት በአይነታቸው ተደርድረዋል። ለጆሮ የሚስቡ ትረካዎች፣ ግጥሞችና መነባንቦች እዚህም እዚያም ይደመጣሉ።

አንባቢያን ወደ ተደረደሩት መጽሐፍት እየቀረቡ አይናቸው የሞላውን መጽሐፍ እያነሱ ገለጥ ገለጥ በማድረግ ውስጡን ይመረምራሉ። ቀልባቸው የወደደውን ይዘውም ከመጽሐፍት ሻጮች ጋር ዋጋ ይደራደራሉ። ደራሲያን ሥራዎቻቸውን ያስተዋውቃሉ፣ አታሚዎች የህትመት ውጤቶቻቸውን ለደንበኞቻቸው ያስጎበኛሉ። ይህ እውቀት የሚሸመትበት ንባብና አንባቢ የሚገናኙበት ‹‹ንባብ ለህይወት›› የመጽሐፍትና የምርምር ተቋማት አውደ ርዕይ አጠቃላይ ድባብ ነው ።

ንባብ የዓለምን ጥልቅ ሚስጥር መርምሮ ለመረዳት የሚረዳ መልካም ተግባር ነው። የሰው ልጆችን የእውቀት ደረጃ ወደ ከፍታ የሚወስድና ምክንያታዊ አስተሳሰብ የሚያላብስ ልምድም ነው። ተደጋግሞ “ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል” የሚባለውም ንባብ ለሰው ልጅ ከሚያበረክተው ከፍተኛ ፋይዳ በመነሳት ነው። በማንበብ ስህተትን መቀነስ፤ በንባብ አላዋቂነትን ማጥፋት ይቻላል።

ክረምት ደግሞ አንባቢን ከመጽሐፍት ጋር በብዛት የሚያገኛኝ ወቅት ነው። በርካታ መጽሐፍት የሚታተሙትና ለምርቃት የሚበቁትም በዚሁ በክረምት ወቅት ነው። ለዚህ ዋነኛ ምክንያት ክረምት የአብዛኛው የትምህርት ማህበረሰብ የዕረፍት ጊዜ በመሆኑ ነው። ይህን የዕረፍት ጊዜም በንባብ ያሳልፈው ዘንድ የተጀመረ በጎ ልማድ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም አብዛኛው ከንባብ ጋር የተያያዘ ህይወት የሚመሩት ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የዕረፍት ጊዜያቸውን በንባብ እንዲያሳልፉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። መጽሐፍት የሰውን አዕምሮ የሚገነቡ፤ በአስተሳሰብ የሚለውጡና ትውልድን ለአገር በጎ ሚና ይኖረው ዘንድ የሚቀርፁ በመሆናቸው የንባብ ልምድን የሚያሳድጉ ሥራዎች መዘውተር እንዳለባቸው ይታመናል።

ይህን ታሳቢ በማድረግ በየዓመቱ በክረምት ወራት ላይ የንባብ አውደ ርዕዮች ይዘጋጃሉ። ዘንድሮም ንባብን የተመለከቱ ልዩ ልዩ መርሀ ግብሮች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ ዓመቱን ጠብቆ በዚህ ወቅት የሚካሄደው “ንባብ ለህይወት የመጽሐፍ አውደ ርዕይ” ተጠቃሽ ነው። በአዲስ አባባ ኤግዚቢሽን ማዕከል በየዓመቱ በደማቅ ሁኔታ ይዘጋጅ የነበረውና በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ተቋርጦ የነበረው “ንባብ ለሕይወት የመጽሐፍ አውደ ርዕይ” ዘንድሮ በደማቅ ሁኔታ ከህምሌ 28 አስከ ነሐሴ 2/2014 ዓ.ም ተካሂዷል።

ይህ ዓውደ ርዕይ፤ የመጽሐፍ አሳታሚዎች፣ የመጽሐፍ መደብሮች፣ ደራሲያን፣ የምርምር ማዕከላትና አንባቢውን በአንድ ቦታ ያገናኘ ነበር። የዘንድሮውን የመጽሐፍ ዓውደ ርዕይ ያዘጋጁት የኢትዮጵያ ቤተ መጽሐፍና ቤተ መዛግብት አገልግሎት ከንባብ ለህይወት ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ነው።

በዚህ ልዩ የመጽሐፍትና የምርምር ተቋማት ዓመታዊ ዓውደ ርዕይ ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ አሳታሚዎች፣ ደራሲያንና የምርምር ማዕከላት ተሳትፈዋል። አዳዲስና ከገበያ ጠፍተው የቆዩ መጽሐፍት፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኤሌክትሮኒክስ(ኢ ቡክ) መጽሐፍት፣ የልጆች መማሪያና የተረት መጽሐፍት በዓውደ ርዕዩ ቀርበዋል።

በዚሁ ደማቅ መድረክ ከ50 በላይ አዳዲስ መጽሐፍትም ለምርቃት በቅተዋል። የምርምር ማዕከላትንና አንባቢውን ማህበረሰብ ተሳታፊ ያደረገው ይህ አውደ ርዕይ አንባቢ የሚፈልጋቸውን መጽሐፍት በቅናሽ ዋጋ እንዲያገኝ ምቹ መድረክ ፈጥሯል። አሳታሚዎችም የህትመት ውጤቶታቸውን ለማህበረሰቡ የማቅረብ እድልን እንዲያገኙ አስችሏል። የመጽሐፍ መደብሮች በቅናሽ ዋጋ ለተደራሲያን መጽሐፍትን ማቅርብ ችለዋል። ደራሲያን ከአንባቢያን ጋር የመገናኘትና ስለ ሥራዎቻቸው የመነጋገር ዕድልን ፈጥሮላቸዋል።

ከ1998 ጀምሮ መጽሐፍ በመሸጥ የሚተዳደረው ፍሬው ሙሉቀን በአውደ ርዕዩ ላይ ተሳታፊ ነበር። “ፍሬው የመጽሐፍት መደብር” በሚል በጊዜያዊነት በአውደ ርዕዩ ለማሳያነት በተሰጠው ቦታ ላይ የተለያዩ መጽሐፍትን ይሸጣል። ዓውደ ርዕዩ አንባቢን ከመጽሐፍ ጋር የሚያገናኝና የማንበብ ክህሎትን እንዲያሳድግ የሚረዳ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ፍሬው ይናገራል።

‹‹ንባብ ትውልድን መቅረፅ የሚችል ትልቅ ጉዳይ በመሆኑ በስፋት ሊሰራበት ይገባል፣ ይህም አንባቢ ትውልድ እንዲፈጠር ያስችላል›› የሚለው ፍሬው፣ አሁን ላይ አልፎ አልፎ የሚካሄዱ የመጽሐፍ ዓውደ ርዕዮች በስፋት ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ይገልፃል።

ሳር ቤት አካባቢ በሚገኘው የመጽሐፍት መሸጫ ሱቁ ለአንባቢያን በመደበኛነት የተለያዩ መጽሐፍትን እንደሚያቀርብ የሚናገረው ፍሬው፤ በዓውደ ርዕዩ ላይ የተለያዩ መጽሐፍትን በቅናሽ ዋጋ ለደንበኞቹ እና ለዓውደ ርዕዩ ተሳታፊዎች አቅርቧል።

በዓውደ ርዕዩ ላይ በተደጋጋሚ መሳተፉንና የዘንድሮው ከሌላው ጊዜ በተሻለ በርካታ ተሳታፊ እንዳለም አስተያየቱን ሰጥቷል። የማህበረሰቡ የማንበብ ልምድ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ቢሄድም አሁን ላይ በህትመት ውጤቶች ላይ እየታየ ያለው የህትመት ዋጋ ጭማሪ አንባቢውን ከንባብ እንዳያርቀው ስጋቱን የሚገልፀው ፍሬው በዚህ ጉዳይ ላይ መሥራት እንደሚገባ ይናገራል።

“ማንበብ ብዙ ዕውቀት መቅሰሚያና እራስን ለማነፅ ተመራጩ መንገድ ነው” የሚለው ፍሬው የንባብ ባህልን በተመለከተ ያለውን ችግር መቅረፍና አንባቢ ማህበረሰብ መፈጠር እንደሚገባ ያምናል። ለዚህ ደግሞ ልጆች ከትምህርት ቤት ጀምሮ የንባብ ፍቅር እንዲያድርባቸው የሚያስችል ሰፊ ሥራ መሠራት አለበት ይላል።

ደራሲ ምግባር ሲራጅ በዓውደ ርዕዩ ላይ ከተሳተፉ ጸሐፊያን አንዱ ነው። አንባቢን ከደራሲያን ጋር ባገናኘው ዓውደ ርዕይ ላይ የራሱንና በሌሎች ደራሲያን የተዘጋጁ መጽሐፍትን ደርድሮ ከአንባቢዎች ጋር ያወጋል። ንባብ ዓለምን መለወጥ የሚቻልበት ትልቅ መንገድ መሆኑን የሚናገረው ይህ ደራሲ፤ አንባቢና መጽሐፍት በስፋት የሚያገናኙ መሰል መድረኮች በስፋት እንደሚያስፈልጉ ያምናል።

አንባቢው መጽሐፍትን አንብቦ ከደራሲው ጋር ስለ መጽሐፉ ለመወያየት እንዲሁም ለመማማርና ጥሩ የሀሳብ ልውውጥ ለማድረግ አውደ ርዕዩ ጥሩ መድረክ እንደሆነም ይናገራል። በተለይም መድረኩ መጽሐፍቱ ላይ ደራሲው እራሱ ፈርሞ ለአንባቢያን ሲሰጥ የሚፈጥረው ጥሩ ስሜት ለማንበብም ጥሩ ማነሳሳት እንደሚሆን ያስረዳል። ደራሲያንም ከአንባቢው በሚሰጣቸው ቀጥተኛ አስተያየት ለቀጣይ ሥራዎቻቸው ትልቅ ልምድና ግብዓት በመድረኩ እንደሚያገኙ ተናግሯል።

ንባብ ትውልድን ስለአገሩ በጎ እሳቤ እንዲኖረውና ለአገሩ መልካም ነገር ማበርከት እንደሚገባው መማሪያ መንገድ ነው። በዚህ መንገድ ትውልድን ለመቅረፅ ደግሞ የንባብ ክህሎትን ለማሳደግ መስራት ያስፈልጋል። ለዚህም አንባቢያን መጽሐፍትን በቀላሉ የሚያገኙበት መሰል መድረኮች መፈጠራቸውና መኖራቸው ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን ደራሲው አስተያየቱን ሰጥቷል።

ዘንባባ እና ትርንጎ የተሰኙ ሁለት የራሱ መጽሐፎች እዚያው አውደ ርዕይ ላይ ይዞ የቀረበው ደራሲ ምግባሩ፤ መጽሐፍቱን ከመደበኛው ዋጋ ባነሰ ለአንባቢያን አቅርቧል። መጽሐፍትን የተመለከቱ ልዩ ልዩ የውይይት መድረኮች ከዚህ በፊት በነበሩ ዓውደ ርዕዮች ላይ እንደነበር በማስታወስም በዘንድሮው አውደ ርዕይ መጽሐፍት ላይ የሚደረጉ ውይይቶች መቀዛቀዛቸውን እንደታዘበም ተናግሯል። በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁ መጽሐፍት ከነ ደራሲዎቻቸው መቅረባቸውንም እንደ አንድ መልካም ተሞክሮ ይጠቅሳል።

ሚኪያስ አቤ በዚሁ አውደ ርዕይ ላይ ‹‹ሀሁ›› በተሰኘ መጽሐፍ መደብር ስም የተለያዩ መጽሐፍትን ለደንኞቹ በማቅረብ ተሳታፊ ነበር። ዓውደ ርዕዩ መዘጋጀቱ መልካም መሆኑን ገልፆ ከሌላ ጊዜ አውደ ርዕዮች በተሻለ መልኩ የተለያዩ መጽሐፍት ይዞ መቅረቡን ይናገራል። የተለያዩ ልቦለዶች፣ ግጥሞች፣ የወግ መጽሐፍት ከ20 እስከ 50 በመቶ የዋጋ ቅናሽ በማድረግም ለገበያ አቅርቧል።

ከመደበኛ የሽያጭ ዋጋ በተለየ ዓውደ ርዕይ ላይ የዋጋ አስተያየት መደረጉና መጽሐፍት በተፈለገው ልክና ብዛት መቅረባቸው አንባቢው ለማንበብ ከመነሳሳት ባለፈ በቀላሉ ለመግዛት የሚችልበት እድል እንደፈጠረ ሚኪያስ ያስረዳል። አንባቢው የዋጋ ቅናሹን ምክንያት አድርጎ መጽሐፍት እየገዛ እንደሆነም ከታዘበው ተነስቶ ይናገራል።

በአውደ ጥናቱ ላይ የተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በጽሑፎችና በመጽሐፍት እንዲሁም በጽሑፍ ክህሎት ላይ የተሠሩ ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን አቅርበዋል። አንባቢያንም በተለያዩ መጽሐፍትና ጽሑፎች ላይ የታተሙ የጥናት ውጤቶችን ለመዳሰስ ምቹ እድል ተፈጥሮላቸዋል። ትምህርትና ጥናት ተኮር ህትመቶቹ በአውደ ርዕዩ ላይ መቅረባቸው ከዚህ ቀደም ከነበረው ልምድ የተለየና መልካም ተሞክሮ መሆኑ ተሳታፊዎች ጠቁመዋል።

የአውደ ርዕዩ መከፈት ስትሰማ ወደ ኤግዚቢሽን ማዕከል በማቅናት መጽሐፍቶችን የሸመተችው ማህሌት ዳኘ፣ ከመደበኛው የተለየ የዋጋ ቅናሽ መኖሩና መጽሐፍት በብዛት መገኘታቸው ለአንባቢ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ታስረዳለች።

‹‹እንደ ማህበረሰብ የማንበብ ልምዳችን አነስተኛ በመሆኑ ንባብ ላይ ጠንክረን መሥራት ይኖርብናል›› የምትለው ወጣት ማህሌት አንባቢን እንደ ብርቅ የሚያይ ማህበረሰብ ስለንባብ ያለው የተዛባ አመለካከት ሊለወጥ እንደሚገባ ተናግራለች። መሰል አውደ ርዕዮች በብዛት ሊኖሩ እንደሚገባ የምትጠቁመው ማህሌት፤ በዓመት ሳይሆን በየወሩ መዘጋጀት እንዳለበት ታስረዳለች። ተመሳሳይ አውደ ርዕዮች አንባቢያን የማንበብ ፍላጎታቸው ከፍ እንዲልና የሚፈልጉትን መጽሐፍ እንዲያገኙ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል ብላም ታምናለች። በህትመት ውጤቶች ላይ የታየው የዋጋ ጭማሪ ግን ለንባብ ክህሎት መዳበር አሉታዊ ሚና እያሳደረ በመሆኑ ሊስተካከል ይገባል ባይ ነች።

በዋጋ ጭማሪው ላይ የመጽሐፍ አሳታሚዎች፣ አንባቢዎችና መጽሐፍ መደብሮችም ተመሳሳይ አስተያየት አላቸው። ለንባብ የተሰጠውን ትኩረት ከፍ ማድረግና ጠቀሜታውን ተረድቶ ዘርፉን በትኩረት መደገፍ እንደሚገባም የበርካቶች እምነት ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የስጦቴ መከራ

ሰላማዊት ውቤ

«በእኛ አካባቢ አካል ላይ የሚደርስ ጉዳት በእርግማን የሚመጣ ዓይነት ተደርጎ ይቆጠራል። ከዓመታት በፊት በእግሬ ላይ የደረሰው አደጋም በወላጆቼ እንደ ፈጣሪ ቁጣ ነበር የታየው። በዚህ ምክንያት በአካባቢው ሰው መዘባበቻ መሆንን ያልፈለጉት ወላጆቼ እቤት ውስጥ ደበቁኝ። አደጋው ሲደርስብኝ ጀምሬው የነበረውን የአምስተኛ ክፍል ትምህርት ለማቋረጥ ተገድጄ ቆየሁ። » በማለት ታሪኳን ያጫወተችን ታዳጊ ተማሪ ስጦቴ ሽለሙ ነች።

ስጦቴ 14 ዓመቷ ሲሆን፤ አሁን ላይ የምትኖረው ከአዲስ አበባ ከተማ 326 ኪሎ ሜትር በስተ ደቡብ አቅጣጫ ሲጓዙ በምትገኘው በከምባታ ጠምባሮ ዞን ውስጥ ባለች ሶያሜ ቀበሌ ውስጥ ነው።

ስጦቴ እንደነገረችን፤ በአካባቢው እሷ ብቻ ሳትሆን በርካታ አካል ጉዳተኞች አካላቸው ላይ በደረሰ የእግር ጉዳት ምክንያት ቤተሰቦቻቸው እቤት ውስጥ ስለሚደብቋቸው የትምህርት ዕድል የሚያገኙበት ሁኔታ እጅግ የጠበበ ነው። እኔ ከእነዚህ አካል ጉዳተኞች መካከል አንዷ ነኝ እንጂ ብዙዎች በዚያ አሉ። ስጦቴ በወላጆቻቸው የተዛባ አመለካከት ምክንያት የትምህርት ብቻ ሳይሆን የሕክምና ዕድልም የሚፈልጉ በርካቶች እንደሆኑ ታነሳለች።

ስጦቴ የእግር ጉዳቱ የደረሰባት ከዓመታት በፊት ነበር። ጉዳቱ ሲደርስባት የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። አምስተኛ ክፍል እያለች ስጦቴ በድንገት አዳልጧት ትወድቃለች። ስትወድቅ በደረሰባት አደጋ ከጉልበቷ በታች አጥንቷ ሙሉ በሙሉ ደቀቀ። ጉዳቱ የእግሯን ሥጋ በልቶታል። የውስጡ አጥንት እስከሚታይ ዘልቆ ገብቷልም። ሆኖም ቤተሰቦቿ ይሄን እያዩ ምንም ሊያደርጉላት አልቻሉም። በእግሯ ላይ የደረሰው ጉዳት እንደ ፈጣሪ ቁጣና ማእት አድርገው መውሰዳቸው ደግሞ ጥረታቸውን እንዲቀንሱ አድርጓቸዋል። ፈጥነው ወደ ሆስፒታል አለመውሰዳቸውም የዛሬውን ማንነቷን



ተማሪ ስጦቴ

ሰጥቷታል። በእርግጥ ለዚህ ምክንያት ነበራቸው። የእሷን እግር ለማሳከም የሚያስችል ገንዘብ አልነበራቸው። ምክንያቱም በእርሻ ቢተዳደሩም ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ ብቻ ነው።

የቤታቸው ጎዶሎ የሚሞላው እነርሱ ለፍተው ከሚያገኙት በተጨማሪ በአካባቢው ሕብረተሰብና በአካባቢው በተለያዩ ልማት ሥራዎች በሚንቀሳቀስ አንድ ግብረ ሰናይ ድርጅት ድጋፍ ነው። ስለሆነም ከዚያ አልፈው ሊያደርጉላት የሚችሉት ነገር አልነበራቸውም። በሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል እንዲሁም በአዲስ አበባ ኪዩር ሆስፒታል የተሻለ ሕክምና ማግኘት እንድትችል ግን ጥረዋል።

በሆስፒታሎቹ በእግሯ ውስጥ የነበሩ የደቀቁ አጥንቶች ተለቅመው ቢወጡም እግሯን ወደ ነበረበት ለመመለስ አስቸጋሪ ሆኗል። ስለዚህም ወደ ቤቷ ተመልሳ በቤቷ ውስጥ ስታዘግም ቆይታለች። ለዓመታት ቤት ውስጥ ደብቀዋትና ከትምህርት ተቆራርጣም ቆየች። እነዚህ ጊዜያት ደግሞ ለእርሷ ተስፋ አስቆራጭ ነበሩ። ቤተሰቦቿም የነበራቸው ስሜት ተመሳሳይ ነበር።

ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንኳን ለመንቀሳቀስ በአራት ሰው የሚደገፍ ቃሬዛ ያስፈልጋት ነበር። በዚያ ላይ የምትኖርበት አካባቢ አቀማመጥ ለአካል ጉዳተኞች አይመችም ። በተፈጥሮ ተራራ መውጣትና ቁልቁለት መውረድ መጠየቁ እንዲሁም ወንዝ መሻገር ማስገደዱ በቃሬዛ የሚሸከሟትን ወላጆቿንና ሌሎች ሰዎችን እጅግ ያማርር እንደነበርም ታስታውሳለች።

ምሬቱ ግን አንድ አጋጣሚን የፈጠረ ይመስላል። የወጣት ስጦቴ ሽለሙን ሕይወት የሚቀይርም ነው። በአንድ ግብረሰናይ ድርጅት አማካኝነት ጥሩ ህክምና ማግኘት ሲሆን፤ ስጦቴ የደረሰባት ችግር የእግዜር ቁጣ ሳይሆን ሁሉም ላይ ሊደርስ የሚችል አጋጣሚ መሆኑን ያስረዳም ነው። ምክንያቱም በወቅቱ ባለሙያዎቹ ተደጋጋሚ ምክር ለአካባቢው ማህበረሰብ መስጠት ጀምረዋል። በዚህ ደግሞ ስጦቴም ተንፈስ ብላለች። ከዚያም አልፋ ስለትምህርቷ ማሰብ እንድትጀምር ሆናለች።

በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ካቋረጠችበት ለመቀጠል የሚያስችላትን ዝግጅት እያደረገች ነው። ከአንዳንድ ተማሪዎች ጋር መተዋወቅ፤ ጓደኛ ማፍራትና ለዓመታት አቋርጣው ከነበረው ትምህርት ጋር በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እራሷን ማለማመድ ጀምራለች። አልፎ አልፎም በአካባቢው በተገነባው የሕዝብ ቤተ መጽሐፍት ትገባና የሚጠቅሟትን ሀሳቦች ትሰንቃለች።

አሁን ላይ በእጅጉ ደስተኛ ናት። ከገባችበት የተስፋ መቁረጥ አባዜ ተላቃለች። ወደፊት የሚታያትም ተስፋ ብሩህ ሆኗል። ከደረሰባት መከራ ብዙ ተምራለች። አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ እና መገለልንም ኖራበታለች። ትምህርት ካለማግኘት አንስቶ እስከ ሥራው ዓለም ድረስ ለአካል ጉዳተኞች ብዙ የሚከብዱ ነገሮችን እንዳሉም አይተዋለች። ለአካል ጉዳተኞች ተብለው የሚዘጋጁ የትምህርት ማሚያ መጻሕፍት አቅርቦትና የትምህርት ዕድል የማግኘት አጋጣሚውም በጣም ጠባብ መሆኑን ተገንዝባለች። ይህ ደግሞ በትምህርታቸው ገፍተው የሚሄዱ የአካል ጉዳተኞች ቁጥር እየመነመነ እንደሚመጣም ታስረዳለች።

በቅርቡ የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የአካል ጉዳተኞች ሪፖርት እንደሚያመለክተው፤ በዓለም ላይ ካሉት አንድ ቢሊዮን አካል ጉዳተኞች መካከል 15 በመቶዎቹ በታዳጊ ሃገራት የሚገኙ ናቸው። ከኢትዮጵያ ህዝብም 20 በመቶ የሚሆኑት አካል ጉዳተኞች ናቸው። ሆኖም ይህ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የህብረተሰብ ክፍል በርካታ ውስብስብ ችግሮች አሉበት። ለዚህ ዋነኛው መንስኤው ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ በቂ መረጃ አለመኖርና አለማግኘት ሲሆን፤ በዚህም ብዙ የአካል ጉዳተኞች ከልጅነታቸው ጀምሮ ይገለላሉ። በየቤቱ ተደብቀው የሚያድጉ አካል ጉዳተኛ ልጆች ከማህበረሰቡ ጋር ከተቀላቀሉ በኋላ መድሎና መገለል ይደርስባቸዋልም። ብዙ ሁኔታዎችም አልጋ በአልጋ አይሆኑላቸውም። እነዚህ ችግሮች ሁሉንም አካል ጉዳተኞችን የሚያጋጥሙ ቢሆኑም በሴቶች ላይ ግን ይብሳል። ከቤት መውጣት አይፈቀድላቸውም። እንደውም እርባና እንደሌላችው ይቆጠራሉ። እነዚህን ተግዳሮቶች ቢያልፉ እንኳን አካባቢያቸው ምቹ አይሆንላቸውም።

አካል ጉዳተኞችም ቢሆኑ ለራሳችው ያላችው ዝቅተኛ አመለካከት ችግሩን እንዲባባስ የሚያደርገው መሆኑን መረጃው ያመላክታል። አቅማቸውን እንዲጠራጠሩ ያደርጋሉ። ለዚህ ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች በቂ መረጃ አለመኖሩ ዋና መንስኤ እንደሆነም መረጃው ያትታል። ስለሆነም ለአካል ጉዳተኞች ተስፋ መለምለም መረጃዎች ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉና ሊሰራባቸው ይገባል። ማህበረሰቡ ላይም ቢሆን ግንዛቤ መፍጠሩ ያላሰለሰ ጥረትን ይጠይቃልና አካል ጉዳተኝነት ተፈጥሯዊ ብቻ ሳይሆን ድንገታዊም መሆኑን አምነን ሁላችንም የበኩላችንን እናበርክት በማለት ሀሳባችንን ቋጨን። ሰላም!!

# ዓለም አቀፍ



## አሜሪካ በአሸባሪው አልሸባብ ላይ የአየር ጥቃት መፈጸሟ ተገለጸ

የአሜሪካ ጦር በሶማሊያ ማዕከላዊ ሒራን ክልል በአሸባሪው አልሻባብ ተዋጊዎች ላይ የአየር ጥቃት መፈጸሙን የሶማሊያ መንግሥት መገናኛ ብዙኃን ዘገበ። መገናኛ ብዙኃኑ እንዳለው ጥቃቱ የተፈጸመው የሶማሊያ መንግሥት ጥያቄ ማቅረቡን ተከትሎ ነው። የአየር ድብደባ ስለመፈጸሙ ግን የአሜሪካ እና አፍሪካ ወታደራዊ ዕዝ አስተያየት አልሰጠም።

የአሜሪካ ባለሥልጣናት በሰኔ እና በሐምሌ ወር በተፈፀሙ ሁለት የአየር ድብደባዎች ሰባት የጂሃዲስት ቡድኑ ተዋጊዎች መገደላቸውን መናገራቸው ይታወሳል። ከቅርብ ወራት ወዲህ አልሻባብ በመንግሥት ኢላማዎች ላይ የሚፈጽመው ጥቃት የጨመረ ሲሆን በቅርቡም ድንበር በመሻገር በኢትዮጵያ ደንገተኛ ጥቃት ፈጽሟል።

አሜሪካ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዜያት በአልሻባብ ቡድን ላይ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን በሰው አልባ አውሮፕላኖች ስትፈጽም ቆይታለች። በተለይም የቡድኑን አመራሮች ኢላማ በማድረግ በፈጸመቻቸው ጥቃቶች ከፍተኛ መሪዎቹን ጨምሮ በርካታ የቡድኑ አባላትን መግደሏን መዘገቡ ይታወሳል።

ሐምሌ 13/2014 ዓ.ም እስላማዊ ታጣቂዎቹ ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር በምትዋሰንባቸው የድንበር ከተሞች የከፈቱትን ጥቃት ተከትሎ ከባድ ውጊያ ተካሂዶ ነበር።

ከአልቃኢዳ ጋር ግንኙነት አለው የሚባለው አልሻባብ ጥቃቱን የፈጸመው ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር በምትዋሰንበት ግዛት በኩል በሚገኙት ዬድ እና አቶ ላይ ነው። ከኢትዮጵያ ጋር በሚዋሰኑት የሶማሊያ ድንበር አካባቢዎች ነበሩ በተባሉ የሶማሌ ክልል ልዩ ፖሊስ አባላት ጋር በተካሄደው በዚህ ከባድ ውጊያም በሁለቱም ወገን ጉዳት መድረሱን የአካባቢው ነዋሪዎች እና ባለሥልጣናት ተናግረዋል።

የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳደር አቶ ሙስጠፌ ዑመርም እስላማዊ ታጣቂ ቡድኑ የከፈተውን ጥቃት የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች መክተው መመለሳቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## የዓለማችን ለኑሮ ምቹ የሆኑ 10 ከተሞች ይፋ ሆኑ



በዓለማችን ለኑሮ ምቹ የሆኑ 10 ከተሞች ይፋ ሆኑ። ከተሞቹ ምርጥ የተባሉት ለኑሮ ባላቸው ምቹነት መሠረት ነው። አውሮፓዊቷ አገር የኦስትሪያ ዋና ከተማ ቪዬና ቀዳሚዋ የዓለማችን ምቹ ከተማ ተብላለች። በተከታይነት ደግሞ የዴንማርክ ኮፐን ሃገን እና የስዊትዘርላንድ ዙሪክ ከተሞች ሁለተኛ እና ሦስተኛ ደረጃን ይዘዋል።

የካናዳ ከተማ የሆኑት ካልጋሪ እና ቫንኩቨር ደግሞ በአራተኝነት በቀጣይ ደረጃ ላይ የተቀመጡ ሲሆን፤ የስዊትዘላንዷ ጄኔቫ፣ የጀርመኗ ፍራንክፈርት፣ የካናዳዋ ቶሮንቶ፣ የኔዘርላንድስ አምስተርዳም፣ የጃፓን ኦሳካ እና የአውስትራሊያዋ ሜልበርን ቀዳሚዎቹን አስር ደረጃዎች ለመያዝ በቅተዋል። ይህንን ደረጃ ይፋ ያደረገው ኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት እንደሚለው ከሆነ ከተሞች ለኑሮ ያላቸው ምቹነት ቢጨምርም ዓለም አቀፉ አማካይ ግን አሁንም ዝቅተኛ ነው ብሏል።

ለኑሮ ምቹነት ከታዩት ጉዳዮች አንዱ የኮሮና ቫይረስ ስርጭት ተጽዕኖ መሆኑን ተጠቁሟል። የዩክሬን ጦርነት ደግሞ ኪዬቭ ከጥናቱ ውጪ እንድትሆን ሲያስገድዳት፣ በሩሲያዎቹ ሞስኮ እና ሴንት ፒተርስበርግ ውጤት ላይም ተጽዕኖ አሳድሯል። በዚሁ ጦርነት ምክንያት የምሥራቅ አውሮፓ ከተሞች ደረጃም ዝቅ ብሏል። የምዕራብ አውሮፓ እና የካናዳ ከተሞች ደረጃውን በመምራት ቀዳሚ ሆነዋል።

ደማስቆ፣ ትሪፖሊ እና ሌጎስ ደግሞ ከማኅበራዊ አለመረጋጋት፣ ሽብር እና ግጭት ጋር ተያይዞ በደረጃው መጨረሻ ላይ ለመገኘት ተገደዋል። በዘንድሮው ጥናት 33 አዳዲስ ከተሞች ተካተዋል። በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ከተሞች ብዙ መሻሻል አላሳዩም ተብሏል። የሶሪያዋ ደማስቆ በደረጃው የመጨረሻው ስፍራን ይዛለች። ቴህራን፣ ዱዋላ፣ ሃራሬ፣ ዳካ፣ ፖርት ሞርስባይ፣ ካራቺ፣ አልጀርስ፣ ትሪፖሊ፣ ሌጎስ እና ደማስቆ ናቸው የመጨረሻዎቹን አስር ደረጃዎች የያዙት።

ለኑሮ ባላቸው ምቹነት መሻሻል ያሳዩ ከተሞችም ታይተዋል። እነዚህ ከተሞች በአብዛኛው በምዕራብ አውሮፓ የሚገኙ የጀርመን፣ የዩናይትድ ኪንግደም እና የፈረንሳይ ከተሞች ናቸው። ፍራንክፈርት ካለፈው ዓመት 32 ደረጃዎችን በማሻሻል ሰባተኛ ደረጃ ላይ ለመቀመጥ በቅታለች። ሃምቡርግ ደግሞ ከ31ኛ ወደ 16ኛ ተመንድጋለች።

የኒውዚላንድ እና የአውስትራሊያ ከተሞች ደግሞ ደረጃው ላይ ማሽቆልቆል አስመዝግበዋል። በዚህም ዌሊንግተን እና ኦክላንድ 46 እና 33 ደረጃዎችን ለመውረድ ተገደዋል። ድርጅቱ ይህን ደረጃ ለማውጣት የከተሞቹን መረጋጋት፣ የጤና ዘርፍ፣ ባህል እና አካባቢ፣ ትምህርት እና መሠረተ ልማት ከግምት ያስገባል። ይህንን ደረጃ ይፋ ያደረገው ተቋም የዩክሬን ጦርነት እና ኮቪድ በሚቀጥለው ዓመት በሚኖረው የከተሞች ለኑሮ ምቹነት ደረጃ ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ብለዋል።

ኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት ላለፉት 70 ዓመታት ኢኮኖሚያዊ ትንታኔዎች በመስጠት የሚታወቀው ሲሆን የዘ ኢኮኖሚስት ጋዜጣ እህት ኩባንያ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ሐሙስ ስፖርት



ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የእግር ኳስ ፌዴሬሽንና የሊግ ኩባንያው ውዝግብ

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከሁለት ሳምንት በኋላ በጎንደር በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባኤ ፌዴሬሽኑን ለቀጣይ አራት አመት የሚመሩ ሰዎችን ይመርጣል። ለዚህም የምርጫ አስፈጻሚና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ባለፈው ግንቦት አዲስ አበባ ላይ ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ መርጦ ወደ ስራ መግባቱ ይታወቃል። ኮሚቴዎቹም ቀደም ብለው ስራቸውን የጀመሩ ሲሆን ከሳምንት በፊትም በምርጫው እጩ ተወዳዳሪዎችን ይፉ ማድረጋቸው ይታወሳል። የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከወር በፊት ስራውን በይፋ ሲጀምር በሰጠው መግለጫ ማንኛውም አካል ምርጫውን በተመለከተ ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ መስጠት እንደማይችል ጠቅላላ ጉባኤው ያጸደቀውን አዲስ የምርጫ ደንብ በመጥቀስ ማብራሪያ ሰጥቶ ነበር።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማህበር የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ማሳሰቢያ ወደ ጎን ትቶ ምርጫውን በተመለከተ ከትናንት በስቲያ መግለጫ ሰጥቷል። ይህም መግለጫ በፌዴሬሽኑ ተቃውሞ የገጠመው ሲሆን ጉዳዩን ወደ ሕግ እንደሚወስደውም ፌዴሬሽኑ በጻፈው ደብዳቤ አሳውቋል።

ውድድር የመምራት እንጂ በምርጫው በድምጽ እንኳን ተሳትፎ የሌለው የሊግ ኩባንያው በኢንተርኮንቴንታል ሆቴል መግለጫ መጥራቱ ተገቢ አለመሆኑን በማሳሰብ ፌዴሬሽኑ የተጠራው መግለጫ እንዲሰረዝ ቀደም ብሎ ደብዳቤ መጻፉ ታውቋል። የሊግ ኩባንያው ይህን ወደ ጎን ትቶ መግለጫውን መስጠቱ ከምርጫው ጋር ተያይዞ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው እስከ ነሐሴ 6/2014 ውሳኔውን እንዲያሳውቅ እየተጠበቀ ባለበት ሰአት ተጽዕኖ እንዳይፈጥር ስጋት ያሳደረ ሲሆን በሁለቱ አካላት መካከል የተፈጠረው ውዝግብም እየከረረ ሄዷል።

ሊግ ኩባንያው መግለጫ ለመስጠት በቦርድ ደረጃ መወሰኑ ከውድድር ውጪ በፌዴሬሽኑ ሃላፊነት ላይ ጣልቃ መግባቱን እንደሚያሳይ ፌዴሬሽኑ የገለጸ ሲሆን፣ ክለቦችም የሊግ ኩባንያው ከተሰጠው ሃላፊነት በላይ መራመዱን በማየት የተቃውሞ ደብዳቤ ሊጽፉ እንደሚችሉ እየተነገረም ነው። ሊግ ኩባንያው የንግድ ስራ ድርጅት የሚሰራ ተቋም ሆኖ የጠቅላላ ጉባኤ አባል ሳይሆን ስለ ጉባኤውና ምርጫው ማውራት ተገቢ እንዳልሆነም ተቃውሞውን ገልጿል።

ከምርጫው ጋር ተያይዞ ቅሬታቸውን ለፊፋ ያሰሙ ወገኖች ያሉ ሲሆን ካፍም ሆነ ፊፋ እስከ ትናንት ከሰአት በጉዳዩ ላይ ያሉት ነገር የለም። ሶስት አባላት ያሉት የምርጫው ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩን መርምሮ አጠቃላይ ውሳኔውን እስከ ነገ ያሳውቃል ተብሎ ይጠበቃል።

የሊግ ኩባንያው ፕሬዚዳንት መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ በሰጡት መግለጫ "ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ውጪ በሌላ ወገን መፍትሄ ለማምጣት የሚሯሯጡ ካሉ አይሆንም ሀገር የሚያስቀጣ ድርጊት ነው" ሲሉ ተናግረዋል። በኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን መረጋጋትና ሰላም ሲኖር የሊግ ኩባንያው ህልውና እንደሚረጋገጥ የገለጹት መቶአለቃ ፍቃደ፣ የሊጉ የስራ አመራር ቦርድ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ከምርጫው ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች ወደ ሊጉ እንዳይመጡና መስተካከል እንዳለባቸው ለስፖርት ቤተሰቡ እንዲገለጽ መወሰኑን ተከትሎ መግለጫው እንደተሰጠ አስረድተዋል።

"ሱፐር ስፖርት በሄደባቸው አገራት መሃል በሊጉና በፌዴሬሽኑ መሀል አለመግባባት ሲፈጠር ከየሀገሩ ጥሎ ወጥቷል" ያሉት መቶ አለቃ ፍቃደ፣ ለዚህም ኬንያና ናይጄሪያ ምሳሌ መሆናቸውን ገልጸዋል። የመግለጫው አንኳር በፌዴሬሽኑ ላይ የታየው የአሰራር ክፍተትና በምርጫው ላይ የፈጠረው ጫና ወደ ሊጉ እንዳይወርድ መሆኑንም አስረድተዋል። በፌዴሬሽኑ በኩል የታዩ እንከኖችንም በዝርዝር ጠቅሰዋል። ምርጫው በተቃረበበት በዚህ ወቅት ስለፌዴሬሽኑ ችግር ማውራት የአቶ ኢሳያስ ጅራን የመመረጥ እድል ለማጥበብ አይመስልም ወይ? በሚል ከጋዜጠኞች ጥያቄ የቀረበላቸው መቶ አለቃ ፈቃደ ምላሽ ሲሰጡም" እኛ ሌላ ሃሳብ የለንም፣ የተፈጠሩ አስተዳደራዊ ችግሮች ወደ ሊጉ እንዳይመጡና የሚመጣው አመራር እጁን እንዲሰበስብ ለማድረግ ነው፣ እንደተቋም ለኳሱ የሚጠቅመው እገሌ ነው ብለን በይፋ የመናገር መብት አለን፣ አሁን ግን የመቀስቀስ ሃሳብ የለንም" ብለዋል።

"ማንንም ይምጣ ማንም በምርጫው ስጋት የለብንም፣ አሁን የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን በተመለከተ ለአንዳቸውም አናደላም፣ ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ ይስጥ፣ የተሰጠውን ድምጽ አንቀበልም አንልም፣ የመግለጫ ጊዜውን በተመለከተ ለእኛ አሁን ጊዜው ነው፣ ምርጫው የሊጉን ሕይወት ይወስናል፣ የምትመርጡትን አመራር ጀርባ አጥኑና ምረጡ እያልን ነው" ሲሉም አክለዋል።

በፕሬዚዳንታዊ ምርጫው የሚወዳደሩት የኢት.ቡና ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ገዛኸኝን በተመለከተ የተናገሩት የሊግ ኩባንያው ፕሬዚዳንት " የአቶ ገዛኸኝ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ መሳተፍ መብቱ ነው ላቆመው አልችልም ሊግ ኩባንያው ላይ ስላለሁ አንተ አትወዳደርም ማለት አልችልም መግለጫውንም የሰጠሁት ገዛኸኝን ልጠቅም አይደለም እንኳን ለፌዴሬሽን ፕሬዚዳትነት ለሀገር ፕሬዚዳንትነት መወዳደር መብት ነው " ሲሉ አስረድተዋል።

"እንኳንስ የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን ምርጫ ላይ ቀርቶ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርና ፕሬዚዳንቱ ሲመረጡ ወጥተን አደባባይ እንናገር የለ፣ አሁንስ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንታንዊ ምርጫ ላይ ብንናገር ለምን ይገርማል..?" ያሉት መቶ አለቃ ፍቃደ፣ የምርጫ አስፈጻሚና የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አባላት የተመረጡት የማይጣሰውን የፊፋን ሕግ ጥሰው መሆን ተናግረዋል። ስለ ችግሩ መፍትሄ የተጠየቁት መቶ አለቃ ፈቃደ "ቁጭ ብለን ተነጋግረን ተወያይተን ችግሩን ገምግመን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ከተዘጋጀን መፍትሄ ይመጣል ነገር ግን ካልተስማማን ፊፋ ይዳኘናል" ብለዋል።

የፌዴራል መንግሥት የስፖርት ማሕበራት ስራ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 37 1/ነ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሀገር አቀፍ የስፖርት ማሕበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ቁጥር 50/2014 መመሪያ ተሻሽሏል።

ይህ መመሪያ የዓለም አቀፉን የስፖርት ሕግና የኢትዮጵያን ሕጎች ባከበረ መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን የስፖርት ባለድርሻ አካላት መክረውበትና ግበዓት ሰጥተው ስራ ላይ እንዲውል የተደረገ መመሪያ መሆኑን ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል። የስፖርት ማሕበራት የአመራር ምርጫ የሚከናወነው ማሕበራቱ ተስማምተው በተቀበሉት በዚህ መመሪያ መነሻነት በየፌዴሬሽናቸው መተዳደሪያ ደንቦች በጉባኤያቸው ባጸደቁት ደምብ እንደሚመሩ ተቀምጧል።

ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን እየተከናወነ የሚገኘው የፕሬዚዳንትና የስራ አስፈጻሚዎች ምርጫ ሂደት ከወትሮ በተለየ መልኩ ፌደሬሽኑ አስመራጭ ኮሚቴን በማስመረጥ ለሕዝብ ግልጽ አድርጎ ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉን ገልጿል። የተመረጠው አስመራጭ ኮሚቴም ነጻና ገለልተኛ ሆኖ በዕቅድ እየተመራ፣ ግልፅ አሠራር እየተከተለ ሂደቶቹ ላይ ለስፖርት ቤተሰቡ መረጃ እየሰጠ፣ የተወዳዳሪ ዕጩዎች ምዝገባ መከናወኑን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቅርበት እየተከታተለ እንደሚገኝ በመጠቆም በዚህ ሂደት ላይ ምንም ዓይነት ቅሬታ ከየትኛውም አካል እንዳልቀረበለት ከኮሚኒኬሽን ዳይሬክተሩ የተገኘው መረጃ ጠቁሟል።

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY
ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ስምግብ ደሕንነት ሁሉም ኃላፊነት አለበት

**ታምራት ተስፋዬ**

የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ እንደሚያመላክተው፣ ደሕንነቱ ያልተጠበቀ ምግብ በመመገብ በየዓመቱ ከ600 ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች ይታመማሉ። ከአስር ሰዎች አንዱ በየዓመቱ በምግብ ወለድ በሽታዎች ይጠቃሉ። አራት መቶ ሃያ ሺ የሚጠጉት ሰዎችም በምግብ ብክለት ምክንያት ሕይወታቸውን ያጣሉ።

በኢትዮጵያም የምግብ ደሕንነት ጉዳይ እንደ ግለሰብም፣ ማሕበረሰብም ሆነ አገር ከፍተኛ ጫና እያሳደረ እንደሚገኝ መረጃዎች ያመላክታሉ። በዛሬው እትማችንም ምግብን ከማምረት እስከ መጠቀም ያለው ሂደት በኢትዮጵያ ምን ገፅታ አለው፣ የምግብን ደሕንነት ከማስጠበቅ አንፃር ውጤታማ ለመሆንስ ምን ሊደረግ ይገባል የሚል ጥያቄ በማንሳት ከጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር አየለ ተሾመ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

ዶክተር አየለ እንደሚገልጹትም፤ ቀደም ባሉት ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ የምግብ መጠን ማነስና መብዛት ስላለው ሁለንተናዊ የጤና ጉዳት እንዲሁም የተለያዩ ምግቦችን መመገብ ስለሚሰጠው የጤና በረከት ብዙ ሲነገር ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ የምግብ ማነስና መብዛት እንዲሁም መለያየት ሳይሆን ደሕንነቱን ማረጋገጥ እጅግ ወሳኝ ጥያቄ ሆኖ ቀርቧል።

በኢትዮጵያም የምግብን ደሕንነት እንደ ግለሰብም፣ ማሕበረሰብም ፣ ሀገር ከፍተኛ ጫና እያሳደረ የሚገኝ ችግር ነው። ምግብን ከማምረት እስከ መጠቀም ያለው ሂደት ችግሮች የሚስተዋሉበት ነው። ከምግብ ደሕንነት ጋር የተያያዙ ችግሮች ደግሞ በጤና ላይ ተወስነው የሚቀሩ ብቻ ሳይሆኑ በማሕበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ጭምር ጫና የሚፈጥሩ ናቸው።



ዶክተር አየለ ተሾመ

እነዚህ የጤና ችግሮች እንደምናስበው ቀላል አይደሉም። አንዳንዶቹ ጊዜያዊ የሆኑ በቀላል ህክምና የሚድኑ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁንና ለረጅም ጊዜ የጤና ችግር የሚያጋልጡም አሉ። አንዳንዶቹ ከንጥረ ነገር መዛባት እስከ ካንሰር የሚያስከትሉ እና ለማሕበረሰባችን ከፍተኛ አደጋ የሆኑ ናቸው።

የጤና ሥርዓታችን አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከመሸከም አንጻር በራሱ ጫና ላይ እያለ በመሰል መከላከል በሚቻሉ ችግሮች ሌላ ጫና ሊሸከም ፈጽሞ አይገባውም። በአንድ በኩል ስለ ሥርዓተ ምግብ፣ በምግብ እራስን ስለመቻል እና የተመጣጠነ ምግብ ስለመብላት ሲታሰብ በሌላ በኩል ደግሞ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ስለ ምግብ ብክለትም ልዩ ትኩረት መስጠትና ጥንቃቄ ማድረግ የግድ ይላል።

ከአመራረት ፣አጋጋዝ ፣ አሰረጫጨት እና አጠቃቀም ጋር ተይይዞ የምግብ መበከልና መበላሸት ያጋጥማል። ሌላው ቀርቶ የመጠቀሚያ ጊዜያቸውን ለማራዘም ማለትም ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ በሚል እሳቤ ምግቦች በኬሚካል የሚበከሉበት አግባብ ይኖራል። አንዳንዶቹ ምግቦች ደግሞ በእድሜ ምክንያት ሊበላሹ ይችላሉ። መሰል የምግብ ብክለት ማስቀረት እና ደህንነቱን በማረጋጋጥ በቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ ማስገባት እስካልተቻለ ደግሞ አደጋው ከፍተኛ ነው።

የምግብን ደህንነት በማስጠበቅ ሂደት «ከእርሻ እስከ ጉርሻ» ያለው ሰንሰለት ደግሞ ረጅም ነው። በዚህ ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላትም የምግብን ደህንነት ከማስጠበቅ አንጻር ወሳኝ ሚና አላቸው። ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ማድረግና ሃላፊነቱን እስካልተወጡ እና ችግሩን ከምንጩ ጀምሮ እያደረቁ መሄድ እስካልተቻለ ድረስ የሚፈለገውን ውጤት ማግኘት አይቻልም።

በቁጥጥር ብቻ መከላከል የሚቻለው በጣም ጥቂት ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን በቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ እንዲወገዱ በሚደረጉ ምርቶች የሚባክነው የሀገር ሀብት ነው። ይህ እንደመሆኑ ችግሮች እዚህ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ማስቀረት የግድ ይላል።

የምግብ ደህንነት በማስጠበቅ ሂደት አውቆም ይሁን ሳያውቁ ሕገ ወጥ ተግባር የሚፈጽሙ አሉ። ጠንካራ የሆኑ የቁጥጥር ሥርዓት በተለይ አምራቾችን በመደገፍ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን አሟልተው እንዲያመርቱ በማድረግ ሂደት ውስጥ ሁሉም ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል።

ከዚህ ባለፈ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የችግሩ ተዋናይ ሆነው የሚገኙትን ፈር ለማስያዝ እንደ ሀገር ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ያስፈልጋል። በቁጥጥር ሂደት የሚገኙ ችግሮች ፈጣን እልባት መስጠትና ተዋናዮች ላይም ተገቢውን የቅጣት እርምጃ ማስተላለፍ የግድ ይላል።

እንደ ዶክተር አየለ ማብራሪያም፤ የምግብ ደህንነት ችግር የእያንዳንዳንዱን ቤት የሚያንኳኳ ነው። በእያንዳንዱ ቤተሰብ ጎጆ ውስጥ የሚገባ ነው። ይህ ማለት እንደ ግልም ፣ቤተሰብም ፣ማሕበረሰብም ሆነ ሀገር ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ነው።

ከመሰረቱ ያልተስተካከለ ችግር ደግሞ መጨረሻ ላይ መመለስ በጣም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ኢንቨስትመንቱ በጣም ከባድ ነው። አስቀድሞ መከላከሉ በአንፃሩ በጣም ቀላል ነው። በመከላከል ሂደት ውስጥ የሚደረግ ርብርብ እና በጋራ የሚሰሩ የመደጋጋፍ ስራዎችም የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ከፍተኛ አቅም የሚፈጥሩ ናቸው።

የምግብ ደህንነትን ያላማከለ የጤና ስራ ትርጉም አልባ ነው። የጤና ሚኒስቴር ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ ችግሩን በመከላከልና በመቀነስ ረገድ በሥርዓት ምግብ ስትራቴጂ እና ፖሊሲ አስደግፎ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ግንዛቤና መፍጠርና መቆጣጠር ጨምሮ የምግብ ደህንነት ለማስጠበቅ በሚሰሩ የተለያዩ ስራዎችን እያስተባበረና እየደገፈም ይገኛል።

የቁጥጥር ስራዎችም በዘመናዊ በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ እንዲከናወኑ በማድረግ ረገድ በተለይ የላብራቶሪ አቅምን በማሳደግ ረገድ ቀሪ ስራዎችን እያከናወነም ይገኛል። ይሁንና ይህ በራሱ ውጤት አይደለም። ውጤት የሚሆነው ችግሩን ከምንጩ ማድረቅ ሲቻል ነው። በመሆኑም በዚህ ደረጃ መንቀሳቀስ ይገባል። በአጠቃላይ ምግብን ከማምረት እስከ መጠቀም ባለው ሂደት ስራዎችን ይበልጥ ማጠናከር ያስፈልጋል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/